# የማይጠራጠር ክርስቲያን




ጽሑፍ፡- በፖል ሃችንስ

ትርጉም፡- ሐዋዝ ወልደሚካኤል



የመጀመሪያ እትም 1952 ዓ.ም፣

2ኛ እትም 1987 ዓ.ም

3ኛ እትም 2001 ዓ.ም

BIBLE BASED BOOKS

SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት

የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል

# የማይጠራጠር ክርስቲያን ።

## መግቢያ

ይህችን ትንሽ መጽሐፍ « የማይጠራጠር ክርስቲያን » በሚል አርእስት ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ለመተርጐም ያሰብሁበትን አጭር ምክንያት ከዚህ በታች ለአንባቢዎች ስገልጽ በትህትና ነው ።

፩ኛ አንድ ቀን ይህን መጽሐፍ በእንግሊዝኛ ሳነብ ፤ ለብዙ ሰዎች የደህንነት መሰናክሎች ( እንቅፋቶች ) የሆኑትን ሰይጣን በዓለም ላይ አብዝቶ የሚጠቀምባቸውን ነገሮች በጣም ቀላል በሆነ መንገድ ከመግለጹ በላይ ፤ ስለነፍሱ ከልብ የሚጨነቅ ሰው የነፍስ ዕረፍት የሚያገኝበትን ዘዴ ስለሚያስረዳ ፡ በአማርኛ ቢጻፍ ጽድቅን ለሚጠሙ ሰዎች በብዙ እንደሚጠቅም ተረዳሁ ።

፪ኛ በመንፈስ ሁለተኛ የተወለደ ክርስቲያን የክርስቶስ የወንጌሉ ብርሃን በልቡ ከበራለት በኋላ ፤ የክርስቶስ መስቀል ወታደር ሆኖ የመንፈስን ሰይፍ ማለት የእግዚአብሔርን ቃል መጽሐፍ ቅዱስን ይዞ ዕለት በዕለት ከጨለማ ማለት ከኃጢአት ጋር ሲታገል ፤ ክርስቶስን በፍጹም ልቡ የተቀበለ ከሆነ ፤ አሸናፊነትን እንደሚያገኝ በቂ የሆኑና ልቡናን የሚያረኩ ማስረጃዎች ይሰጣል ።

## ማስገንዘቢያ

አንባቢ ሆይ ፡ ይህችን መጽሐፍ ስታነብ ያለህበትን ሁኔታ በመገንዘብና ሰይጣን በመጀመሪያ በአ

ንባቢ ልብ ላይ የሚወረውረውን የንቀት ወይም የማሽሟጠጥን አጥቂ ፍላፃ ፤ « ቆይስቲ መጨረሻውን ማየትና መመርመር አለብኝ » በሚል የቅንነት ጋሻ እየተከላከልህ እንብበህ እንድትጨርሳት ልባዊ ምኞቴ ነው ።

## ምስጋና

ይህችን መጽሐፍ ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ እንድተረጉማት ለፈቀዱልኝ ለምስተር ፖል ሃችንስ (Paul Hutchins) ከልብ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

## እርእስተ ነገሮች


| ምዕራፍ፡ | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፩ |
| ፩ የደህንነት እርግጠኛነት እንቅፋቶች ። . . . . | ፫ |
| ፪ የደህንነት ፍጹም አስፈላጊነት ። . . . . . . . . | ፲፱ |
| ፫ ክርስቲያን ለመሆን እንዴት እንደሚቻል ። . . | ፴፩ |
| ፬ እንዴት እንደምናውቅ ። . . . . . . . . . . | ፵፪ |
| ፭ የማይጠራጠር ክርስቲያን ሕይወት ። . . . . | ፶፩ |
| መደምደሚያ . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፷፩ |






## የደህንነት እርግጠኛነት እንቅፋቶች ።

የዚህች ትንሽ መጽሐፍ ዓላማ ፤ እግዚአብሔር የታወቀና ሊታወቅ የሚቻል መሆኑን ለማሳየት ነው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲጸልይ ፤ « እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት » እንዳለ እግዚአብሔር በእውነት ሊታወቅ የሚቻል አምላክ ነው ።

መቼም ቢሆን የማይታየውን እግዚአብሔርን ያየ አንድ ስንኳ የለም ፤ ነገር ግን ልጁ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ገለጸው ። ምን ጊዜም ቢሆን ኤሌትሪክ ምን እንደሆነ ያየው የለም ። ነገር ግን የኤሌትሪኩ አንፑል እንዲታይ ያደርገዋል ። እንደዚሁም ሁሉ ኢየሱስ « እኔን ያየ አብን አየ » ብሏል ።

« ፍጹም አውቃለሁ » የሚያሰኝ አለኝታ በሚያምን ልብ ይገባል ። እንደዚህ ያለው እውቀት ያንተ ሊሆን ይቻላል ። <u>አሁን</u> የዘላለም ሕይወት እንዳለህ ልታውቅ ትችላለህ ። እንደ ጳውሎስ ማንን እንዳመንህ ልታውቅ ትችላለህ ። ራስን ገዞቅ በማድረግ የሚገኝና የማይጠረጠር ከሁሉ የሚበልጥ አንድነት ከእግዚአብሔር ጋር እንዳለህ ልታውቅ ትችላለህ ። « ራስን ገዞቅ በማድረግ » ያልሁበት ፤ ይህ « እርግጠኛ ነኝ »

የሚባል ነገር ራስን ከፍ ከፍ የማድረግና የኩራት መንፈስ ነው ፤ ይህም ማለት አንድ ሰው መንግሥተ ሰማያት ለመግባቱ እርግጠኛ ሆኖ ሲናገር በራሱ ደግነትና ቅድስና መመከቱ ነው ብለው በልባቸው የሚያስቡ አንዳንድ ሰዎች ስላሉ ነው ።

እንደዚህ ያለው መቃወም የሚመጣው እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል ከለማስተዋል የተነሣ ከመሆኑም በላይ ፤ ደህንነት የሚገኘው በራስ ደግነትና ቅድስና ነው ብሎ ተቃዋሚው ማመኑን በግልጽ ያሳያል ። መጽሐፍ ቅዱስ ብንጥር ብንግር ጽድቃችን ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ እንደሆነ በግልጽ ያስተምረናል ። ደግሞም « ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና ይህም የእግዚአብሐር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም » ይልና ቀጥሎ የሚገኘው ቁጥር ፱ « ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም » ብሎ ያረጋግጥልናል ።
( ኤፌሶን ፪ ፰ና ፱ እይ ። )

እውነተኛና እርግጠኛ አማኝ በሥራው ከቶ አይመካም ፤ ነገር ግን በትሕትና ከጳውሎስ ጋር « ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል (ሞት) በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ » ይላል ። ( ገላትያ ፮ ፲፬ ። )

ይህን መጽሐፍ የጻፍሁት የመቃወም መንፈስ አድሮብኝ ሳይሆን ፤ የጌታ ፍቅር ስላደረብኝ ነው ፤ ደግሞም የሚያነቡት ሁሉ ለደህንነታቸው ፤ ክርስቶስ በፈጸመው ቤዛነት ከልባቸው መመከትን እንዲማሩ ነው ።





ጴጥሮስም መልሶ — ጌታ ሆይ ፤ አንተስ ከሆንህ በውኃው ላይ ወደ አንተ እንድመጣ እዘዘኝ አለው ። እርሱም — ና አለው ። ጴጥሮስም ከታንኳይቱ ወርዶ ወደ ኢየሱስ ሊደርስ በውኃው ላይ ሄደ ። ነገር ግን የነፋሱን ኃይል አይቶ ፈራ ፤ ሊሰጥምም በጀመረ ጊዜ — ጌታ ሆይ ፤ አድነኝ ብሎ ጮኸ ። ወዲያውም ኢየሱስ እጁን ዘርግቶ ያዘውና — አንተ እምነት የጐደለህ ፤ ስለምን ተጠራጠርህ ? አለው ። ወደ ታንኳይቱም በወጡ ጊዜ ነፋሱ ተወ ። በታንኳይቱም የነበሩት — በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው ሰገዱለት ። ማቴ. ፲፬ ፤ ፳፰ — ፴፫ ።

እንግዲህ ሰዎች መዳናቸውን እንዳያረጋግጡ እንቅፋት የሚሆኑባቸውን ነገሮች አንድ ባንድ እንመልከት ።

## በምግባር መመካት

ብዙ « ክርስቲያኖች ነን » የሚሉ ፤ የምንድነው በሥራችን ጭምር ነው እያሉ ስለሚመኩ የመዳን እርግጠኛነት የላቸውም ። ትክክለኛ ኑሮ በመኖርም የዘላለምን ሕይወት የሚገዙ ይመስላቸዋል ፤ በፍርድም ጊዜ መልካም ሥራቸው ክፉ ሥራቸውን የሚመዝን እንደሆን ፤ እግዚአብሔር ደስ ይለውና « አሥን አንተ መልካም ባርያ የታመንህም » ብሎ የሚቀበላቸው ይመስላቸዋል ። ነገር ግን ደኅንነት አስቀድሞ በከበረው በክርስቶስ ደም ሁነዋልና ዘላለማዊ ሕይወት የሚሰጠው ለሚያምኑ ብቻ ነው ። ( ሮሜ ፮ ፳፫ ፡ ዮሐ. ፫ ፴፮ ፡ ) ስለ ዚህ እግዚአብሔር አስቀድሞ በጸጋው የሰጠንን እኛ ለመግዛት አንችልም ። በክርስቶስ ፍጹም ሥራ ላይ ምንም ነገር ልንጨምርበት አንችልም ። ፍጹምነት በሌለው ሥራችን ዕዳችንን ከፍለን በርሱ ዘንድ ሞገስ (ጸጋ) እናገኛለን በማለት እንዳንሰድበው ።

ለመሆኑ ፤ መንግሥት ሰማያት የምንገባው በሥራችን ነው ቢባል ፤ በቂ ሥራ ሠራን የምንልበትን ጊዜ እናውቀው ይሆን ? ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ፤ የጸሎት መጽሐፍ በማንበብ ፤ ገንዘብ በመስጠት ፤ ሱባዔ በመግባት ፤ በግብረ ገብነትና ይህን በመሰለ ነገር ሁሉ ራሳችንን



የምናድን ከሆንን እንግዲያው ክርስቶስ በከንቱ ሞተ ፤ እኛም አርዓያ የሚሆነን እንጂ መድኅን አያስፈልገንም ማለት ነው ።

ከክፉ ነገር በመጠበቅ የዘላለምን ሕይወት እናገኛለን ማለት ዘር ሳይዘሩ ፤ እርሻዬ ብዙ አረም የለበትምና ብዙ የስንዴ ሰብል እሰበስባለሁ ብሎ እንደሚጠባበቅ ሞኝ ገበሬ መሆን ነው ።

በምግባር ለመዳን ይቻላል ብሎ የሚያስተምር ሃይማኖት ሐሰትን የተጐናጸፈ ሃይማኖት ነው ። በዓለም የሚገኙ የግብረ ገብነትን ትምህርት የሚያስተምሩ የሐሰት ሃይማኖቶች ሁሉ ፤ ሰው የእግዚአብሔርን ምሕረት የሚያገኝበት አንድ ነገር መሥራት ይችላል የሚል ትምህርት ያስተምራሉ ። እነዚህ ያለ ክርስቶስ የሆኑ ሃይማኖቶች « መልካም ሥራ ብንሠራ በመጨረሻ ምናልባት እንድን ይሆናል » ይላሉ ።

እውነተኛ ክርስትና እንዲህ አያስተምርም ። በክርስቶስ እምነን አሁኑኑ መዳን ነው ። ከዚያ በኋላ ስለዳንን መልካም ሥራ እየሠራን በጽድቅ እንኖራለን ። እንዲህ ከሆነ መልካም ሥራ ከደህንነት በኋላ የሚገኝ ፍሬ ነው እንጂ የደህንነት መገኛ አይደለም ፤ ይህም ማለት መዳናችንን ለማሳየት መልካም ሥራ እንሠራለን እንጂ እንድንበቃለን ብለን እንሠራም ።

ደህንነት የክርስቲያን ሕይወት መሠረት ነው ። ወደ ፊት ያውም ገና ለምናልባቱ እድንበቃለሁ ብሎ

መልካም ሥራ መሥራት ፤ መሠረቱን በጣሪው ላይ አድርጎ ቤት ለመሥራት እንደመሞከር ይቆጠራል ።

ወዳጄ ሆይ ፤ የቻልነውን ያህል እንሠራለን ብለን ብንጥር ከቶ ልንድን አንችልም ። ለምን ? የሚል ጥያቄ ቢመጣ ለዚህ መልሱ በጣም ቀላል ነው ፤ ፍጹማን መሆን ስለማንችል ነው ። በዚህ ምክንያት ክርስቲያን ነኝ ብሎ በአፉ ብቻ ለሚናገር በውስጡ የመዳኑን ምስክርነት እግዚአብሔር አይሰጠውም ። በኤፌሶን ፪ ፰፡፱ ። « በጸጋው ድናችኋልና በሃይማኖት ይህም ከእናንተ አይደለም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው በምግባር አይደለም ማንም እንዳይመካ » የሚለውን ቃል ለሚቃወም ሁሉ ፤ እውነተኛውን የመዳንን እርግጠኛነት በውስጣችን የሚሰጠን የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ነውና ፤ መንፈስ ቅዱስ ድነሃል ብሎ አይመሰክርለትም ።

## ሃይማኖታዊ ነኝ ብሎ መመካት

በቤተ ክርስቲያን አባልነት ወይም የአንድ የሃይማኖት ማኅበር ወገን በመሆን መመካት ፤ እውነተኛ ክርስቲያን የሚያገኘውን ሙሉ ሰላም እንዳያገኙ ለብዙ ሰዎች በዚህ ፈንታ የሐሰት ሰላም ሰጥቷቸዋል ። እነዚህም ሰዎች ጸሎት ያደርጋሉ ፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ ፤ ይዘምራሉ ፤ የእሑድ ትምህርት ያስተምራሉ ፤ እንዲያውም በጉባዔ ፊት ይጸልያሉ ። ነገር ግን ይህ ሁሉ ሲሆን በራሴ ደርሶ እንዳየሁት ፤ ሥራቸው ሁሉ



እውነተኛ የመንፈስ ፍሬ ሳይሆን በውጭ ብቻ የሚታይ ገለባ ነው ።

ሃይማኖት የሌለው ሰው አይገኝም ። ሃይማኖት የለኝም የሚል ሰው እንኳ ቢገኝ ፤ ትንሽ የሃይማኖት ፍልስፍና ከገዛ ራሱ ወይም ከሌላ ያገኘውን ያልያዘ አይገኝም ። ይህችም ፍልስፍና ከፉ ነገር በሠራ ጊዜ ከሚመጣበት የሕሊና ወቀሳ ለጊዜው መጠጊያ ትሆነዋለች ። ሃይማኖት ማለት እኮ በውስጣዊ ስሜትና በአፍአዊ የነፍስ ሥራ የሚገለጽ የሕይወት ፍልስፍና ነው ።

አረመኔዎችም እንኳ « ሃይማኖታውያን » ናቸው ፤ ነገር ግን ክርስቲያኖች ናቸው ብሎ የሚያስብ ማንም የለም ።

ክርስትና ወይም ክርስቲያንነት በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ ብቻ የምትሰጥ ናት ። « በአንጾኪያም አስቀድሞ ደቀ መዛሙርት ( አማኞች ) ክርስቲያን ተባሉ ። » ( የሐዋርያት ሥራ ፲፩ ፳፮ ። )

የምንድነው በሰው ሰራሽ ሃይማኖት ወይም በክርስትና በማመን አይደለም በአንድ ሰው እንጂ እርሱም ክርስቶስ ። ከኃጢአት የምታድነን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አይደለችም የቤተ ክርስቲያኒቱ ክርስቶስ እንጂ ። መጽሐፍ ቅዱስ « በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን ትድናለህ » ይላል እንጂ በሰው ሃይማኖት ወይም በክርስቲያንነት እመን ትድናለህ አይልም ። ( የሐዋ.፲፮ ፴፩ ። )

አስተውል ፡ በኛ ምትክ ሆኖ መከራን የተቀበለ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነው እንጂ ፤ የሰው ሃይማኖት ወይም ቤተ ክርስቲያን በመስቀል ላይ አልሞተልንም ። ለሰው ምትክ የሚሆን ሰው ብቻ ነው እንጂ የሰው ሕንፃ ወይም ሃይማኖት አይደለም ። ስለዚህ የሚያስደንቅ ተውላጣዊ ቤዛ የተዘጋጀልን ለኛ ተለዋጭ ሆኖ በሞተልን በክርስቶስ ነውና መድኅን እርሱ ብቻ መሆን አለበት ። እንዲህ ከሆነ ማድረግ የሚገባህ ክርስቶስን መቀበል እንጂ ሃይማኖታዊ መሆን አያሻህም ። ክርስቶስን በእምነት ዓይን ስታየው ፡ ያን ጊዜ ክርስቲያን ትሆናለህ ፤ በዚያች ሰዓት ለመዳንህ እርግጠኛ ትሆናለህ ፤ የማይጠራጠር ክርስቲያን ትሆናለህ ።

ምንም የብዙዎች ሰዎች መመለስ ታሪካቸው በሐዋ. ሥራ ተጽፎ ቢገኝ ታሪካቸው በዝርዝር የተጻፈ ክርስቲያኖች ሦስት ብቻ ናቸው ። እነዚህም የጠርሴሱ ሳውል ( ጳውሎስ የተባለውና ) ኢትዮጵያዊው ጃንደረባና ቆርኔሌዎስ ናቸው ። ከእነዚህም እያንዳንዳቸው ክርስቲያኖች ከመሆናቸው በፊት ሃይማኖታውያን መሆናቸው ጉልህ አይደለምን ? በነዚህ ሃይማኖታውያን በነበሩ ሰዎች ታሪክ እንዳየነው በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ መዳን ፍጹም አስፈላጊ እንደሆነ መንፈስ ቅዱስ ገልጾልናል ። እነዚህ ሰዎች በድሮው ሥራቸው ቢቆዩ ኖሮ ባልዳኑም ነበር ፡ ስለዚህ ለእኛ ይህ ታላቅ ምሳሌ አይሆንምን ?

## ስሜትን መደገፍ

ከኃጢአት መመለስና እንደገና መወለድ ማለት ምን እንደሆነ በለማስተዋል ፤ አንዳንድ ለመጽደቅ



የሚፈልጉ ሰዎች በውስጥ የተለየ አንድ ነገር እስኪሰማቸው ድረስ እግዚአብሔር ስለ ዘላለም ሕይወት የሰጠውን ተስፋ ለማመን ይፈራሉ ። ይህም የሚሆነው ክርስቲያኖች ስለ ደኅንነት በሚያስገርም አኳኋን በመሰከሩላቸው ጊዜ በጌታ በራሱ በማመን ፈንታ አንድ ነገር በውስጥ እንዲሰማቸው በመፈለግ ነው ከዚህም የተነሣ ወደ ሰላም ሳይደርሱ ተሰናክለው ቀርተዋል ።

ሁላችንም የተለያየ ባሕርይ ስላለን እግዚአብሔር ወደ እርሱ ስንመለስ የሚሰጠን ስሜት አንድ ዓይነት አይደለም ። እንግዲህ ሌሎችን እማኞች ተመልክተን ስሜትን አስቀድሞ በመፈለግ እንዳንታለል መጠንቀቅ ያሻናል ። ያ ክርስቲያን ስሜት ያደረበት በፍጹም ልቡ አምኖ መጽደቁን ካረጋገጠ በኋላ ነው እንጂ በፊት እንዳልሆነ አስብ ። እግዚአብሔር ያቀደው ተርታ መጀመሪያ እምነት ቀጥሎ እርግጠኛነት ከዚያ በኋላ ስሜት ነው ። ሰይጣን እነዚህን ነገሮች እንድናዘዋውራቸው ያደርጋል ማለት መጀመሪያ ስሜት ቀጥሎ እርግጠኛነት ከዚያ በኋላ እምነት ይለናል ። በዚህ ምክንያት ብዙዎቹ የሚፈልጉትን ሳያገኙ በመቅረታቸው ተስፋ ይቆርጣሉ ።

አንድ ጊዜ ጉባዔ ተደርጐ ሳለ ከአንድ ገበሬ ጋር ተዋወቅሁ ፤ ይህ ገበሬ አሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ እግዚአብሔር እንዲያድነው ይጸልይ ነበር ። ነገር ግን በመንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ ነበረና « አይ እኔ ከተመረጡት አንዱ አይደለሁም » እያለ ያስብ ነበር ።

ይህም የሆነበት ምክንያት አማኞች ክርስቲያኖች ምስክርነታቸውን ሲሰጡ ፤ ያም ይመጣና « መላእክት ሲጎበኙን አየሁ ሌላውም እንዴት ያለ ሕልም አየሁ » እያሉ ይደሰቱ ስለ ነበር ነው ፤ ስለዚህ ያም ገበሬ እግዚአብሔር እንደተቀበለኝ የማውቀው እንደዚህ ያለ ምልክት ሳገኝ ነው እያለ በከንቱ ይጸልይ ነበር ።

የዚያኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ ሰውየውን ለማነጋገር ሀያ ኪሎ ሜትር ተጓዝሁ ። በቀላሉ ፩ኛ ዮሐንስ ፭ ፲፫ን ገለጥሁና አሳየሁት ። ክርስቶስን እንደግል መድኃኒቱ አድርጎ እንደተቀበለው እርግጠኛ ነበር ። ነገር ግን « የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ » የሚለው ጥቅስ ምስጢሩ ፈጽሞ አልገባውም ነበር ።

ምንም እንኳን ከፊተኛው የተለየ ስሜት ባይሰማው ፤ ከኔ ጋር ተንበረከከና እግዚአብሔርን ስለ ዘላለማዊ ሕይወት አመሰገነ ። በቅዱስ ቃል ጸንቶ እንዲቆም እግዚአብሔር ይረዳው ዘንድ ለመነ ። ተለይቼው ስሄድ እንኳ ውስጣዊ ምስክር አልነበረውም ። ነገር ግን በልቡ በእግዚአብሔር ልጅ አምኖ ስለነበረ አሁን የዘላለምን ሕይወት አግኝቻለሁ እያለ ይህችን ተስፋ አጥብቆ ይዞ ነበር ።

የዚያኑ ዕለት ማታ ወደ ተሰበሰብንበት ድንኳን መጥቶ እጄን መጀመሪያ የጨበጠ እርሱ ነበር ። ቀና ብሎ እየና በደስታ « መዳኔን አሁን አውቃለሁ እኮ » አለኝ ። እሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ ሲፈልግ



የነበረውን በአምስት ደቂቃ ውስጥ አገኘ ። በጎረቤቶቹ ምስክርነት እምነቱን ከክርስቶስ መስቀል ብርሃንና ከተፈጸመው ቤዛነት መልሶት ነበር ።

ዓይናችን ከኢየሱስ እናንሣ ። የዓለም ብርሃን እርሱ ነው ። እርሱን የሚያውቁ የክርስቲያኖች ብርሃን ግን ጨረቃ ከፀሐይ ወስዳ እንደምታበራው ያለ የሚያብለጨልጭ ብርሃን ነው ።

አንዳንዶቹ ክርስቲያኖች ፀጥ እንዳለ ውሃ ፀጥተኞችና የማይጨነቁ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ከአንዱ ተራራ ጫፍ ወደ አንዱ ተራራ የሚሟሉ ( የሚሳጉ ) ይመስላሉ ። ሌሎቹም በሚያሰክሩ ልዩ ልዩ የውስጥ ስሜቶች በውኃ ሙላት እንደሚወሰዱ ነገሮች ናቸው ። ደስታችን ወይም ሐዘናችን ምንም ዓይነት ቢሆን ፤ በሕይወታችን ባሕር ላይ እየሸበረቀ ወደ ሰማያዊ አባታችን ቤት በደህና የሚመራን ፤ « እኔም የዘላለምን ሕይወት እሰጣቸዋለሁ ለዘላለም አይጠፉም » ተብሎ በዮሐንስ ወንጌል የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ነው ።

ስሜት ያታልላል ። ስሜትን ከተደገፍን ሁል ጊዜ እንጠራጠራለን ።

« ያም መንፈስ ለመንፈሳችን ይመሰክራል እኛ የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆን » ( ሮሜ ፰ ፲፮ ። ) ነገር ግን በዚህ መንገድ ተናገረን ብለን እናስገድደው ።

## ሰላምን በልዩ ልዩ የአእምሮ መንገድ መሻት

ዛሬ ብዙዎቹ ፤ አራሳቸው አስበው በወጡት መንገድ የነፍስን እረፍትና እግዚአብሔርን ለማግኘት

ይለፋሉ ። በዚህ ሳይሆንላቸው ሲቀር በቀላሉ በክርስቶስና በመጽሐፍ ቅዱስ አምነው የልብና የአእምሮ ፅረፍት ያገኙትን ሰዎች በመናቅና በማቃለል ፤ እግዚአብሔር የለም ወይም እንደ ገጽና እንደ አካል ነው እስከ ማለት ይደርሳሉ ። አንድ የማይጠራጠር ክርስቲያን ስለ መንፈሳዊ ነገር ሊያነጋግራቸው ሲሞክር ፤ እምነት ያለውን ያን ሰው ፤ በስሜቱ ብቻ እንደሚነዳ ይቆጥሩትና «እስቲ ይህንን ዘሐሳቤ ተመራምሬ እንዳየው አድርግ» እያሉ ያሽሟጥጡታል ። ይህንንም ማለታቸው እግዚአብሔር ከሰዎች ነፍሳት ጋር የሚገናኝበትን ዘዴ ካለማስተዋላቸው የተነሣ ነው ። እነዚህ ሰዎች ሥጋዊና መንፈሳዊ የሚባሉ ክፍሎች እንዳሉና እነዚህም ሁለቱ የየፈሳቸው ሕግ ኖሯቸው የተወሰኑ ውጤቶች እንዳሏቸው ለማወቅ የታወሩ ይመስላል ።

የዚህ ዓለም ዕውቀት እንኳን ያለ ሕግ እይከሄድም ። ለምሳሌ አንድ ሰው የሂሳብ ሥራ ለመሥራት ዚፈልግ የተመደበውን የሂሳብ አሠራር (ፎርሙላ) ማጥናት አለበት ያለዚያ ግን አንድ አስቸጋሪ ጥያቄ (ፐሮብሌም) የመጣበት እንደሆነ ዓይኑ ፍጥጥ ይላል ።

<u>በመንፈሳዊውም</u> በኩል ቢሆን ክርስቲያንነት ያለ ሕግ የሚራመድ አይደለም ። እፍታቶ የሚናገር የራሱ መጽሐፍ አለው ፡ እርሱም መጽሐፍ ቅዱስ ። ሕጉም የማይለወጥና የማይሻር ነው ። በገላትያ ፮ ፯—፰ እንደተጻፈው የመዝራትና የማጨድ ሕግ አለ « ሰው የሚዘራውን ያንኑ መልሶ ያጭዳል ። ለሥጋው የሚዘራ



ከሥጋው መበስበስን ያጭዳልና ለመንፈስ የሚዘራ ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል » ።

በሁለተኛ ቆሮንቶስ ፭ ፲፯ « በክርስቶስ የሆነ ሁሉ እርሱ አዲስ ፍጥረት ነው » የሚል ሕግ አለ ። ይህን ነገር ተገንዝቦ በሕይወቱ የሠራበት ሰው ሁሉ ተሰናክሎበት አያውቅም ።

መጽሐፍ ቅዱስ ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነና የሚያምንበት ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዳለው ይናገራል ። ይህንም የሚያምኑ ሁሉ እውነት ሆኖ አግኝተውታል ። ነገር ግን አዋቂዎች ነን የሚሉ ዓይናቸውን ጭፍን አድርገው « እስቲ እውነት ከሆነ ለእኔ በሚመስለኝ መንገድ አሳየኝ » ይላሉ ። የዕውቀታቸውን ማዕድን በመቆፈር ወደ መንፈሳዊ ተራራ ጫፍ ለመውጣት ይሞክራሉ ። በመንፈሳዊ ጨለማ መንገዶች ይጓዙና የትምህርት ወይም የጥበብ ብርሃን መንገዱን ሳያሳያቸው በቀረ ጊዜ ይበሳጫሉ ። ልክ በፊታቸው ያሉትን ነገሮች ለማየት መለስ (ዘወር) ይላሉ ። ማድረግ የሚገባቸው በክርስቶስ የተገለጸውን እውነት መቀበል ብቻ ሲሆን ፤ አሁንም ገና « እውነትን ለማግኘት ይጥራሉ ። » የሕይወት ውሃ በዙሪያቸው በየስፍራው ሲፈስ « እንዲት ጠብታ እንኳ አጣን » ብለው ያጉረመርማሉ ።

አብ « እነዚህን ነገሮች አዋቂዎችና ጥበበኞች ነን ከሚሉት ሠውሮ ለሕፃናት ገለጸላቸው » ብሎ ክርስቶስ የተናገረው ምንኛ እውነት ነው ። የተደበቀባቸውም

ምክንያት ያለ በቃው ለማግኘት ስለሚፈልጉ ነው ። እንደ ሰው በራሱ እእምሮ በፈለሰፈው የነፍሳዊ ኃይል ዘዴ መንፈሳዊው ነገር ይገበኛል ብሎ መሞከርና እውነተኛውን የእምነት መንገድ መናቅ ፤ በመልኩና በውበቱ የሰውን ሕሊና በሚማርክ ፤ በንዚን በሌለው አውቶሞቢል እሄዳለሁ ብሎ እንደማሰብ ይቆጠራል ።

ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ « ሥጋዊ ሰው ግን የእግዚአብሔርን መንፈስ ነገር አይቀበልም በርሱ ዘንድ ስንፍና ነውና ያስተውለውም ዘንድ አይቻለውም በመንፈስ ይፈረድበታልና » እያለ በ፩ኛ ቆሮንቶስ ፪ ፲፬ በግልጽ ይናገራል ። « የመስቀሉ ነገር በጥፎች ዘንድ ስንፍና ነውና ። በኛ ግን በዳነው ዘንድ የእግዚአብሔር ኃይል ነው » ። (፩ኛ ቆሮንቶስ ፩ ፲፰ ።)

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ነገሮች አንድ ግልጽ የሆነ ትርጉም አላቸው ። ሥጋዊ ሰው አስቀድሞ በወንጌል የሚገኙትን ትእዛዛት « አሜን » ብሎ ሳይቀበል በወንጌል እውነትና በደህንነት መንገድ ያስ አይለውም ሊደሰትም አይችልም ። በዓለም ላይ በቀላሉ ለሰው የሚገባ ፤ እላይ ከተጠቀሱት የበለጠ አንድም ነገር የለም ግን በአእምሮ ብቻ ከሚመረምረው ሰው ስውር ነው ። ስለዚህ የጥበብ ( የሳይንስ ) ትምህርት ለአንድ ሕፃን ሞኝነት መስሎ እንደሚታየው ፤ ለሥጋዊውም ሰው መንፈሳዊው ነገር ቂልነት መስሎ ይታየዋል ።

ብዙ እውቀትና ጥበብ ያላቸው ብዙዎቹ በክርስትና ትምህርት አምነው የእግዚአብሔርን ቃል ሲመገቡ ፤



ሌሎቹ ደግሞ እኩል እውቀት ያላቸው ፤ የራሳቸውን ዕውቀት ከማምለካቸው የተነሣ አእምሯቸው በጨለማ ውስጥ እንደ ተሸፈነ ስንመለከት ፤ ሰዎች እግዚአብሔርን የማያውቁት ዐዋቂዎች በመሆናቸው ወይም ባለመሆናቸው ሳይሆን በዮሐንስ ወንጌል ፯ ፲፯ « ፈቃዱን ( የእግዚአብሔር ) ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር . . . ያውቃል » የሚለውን ቃል ባለመረዳት መሆኑን እንገነዘባለን ።

## ክርስቶስን አለመከተል

በእውነት ሁለተኛ እንደ ተወለደ ሰው የሚጨነቅ ያለ አይመስለኝም ። ይህንንም ስል « እዩ እኩነን ይሆን » እያለ ከማመኑ በፊት ይጨነቅ እንደነበረው ይሆናል ማለት አይደለም ፤ ነገር ግን እንዲት የሚወጓት ኃጢአት ትኖርና ያችን በሥራ ቁጥር ፤ ወይም እንደ ሎጥ መንፈስ ቅዱስ የሚገልጽለትን ሥራ ቸል ሲል የተሰጠኝን መንፈስ አሳዘንሁ እያለ ይጨነቃል ማለቴ ነው ። « መልካም ነገርን ማድረግ የሚያውቅ የማያደርገውም ያው ኃጢአት ይሆንበታል » ። ( ያዕቆብ ፬ ፲፯ ። )

የሕይወታችንን ሩጫ ጨርሰን ወደ አምላካችን በሄድን ጊዜ « አንተ መልካምና ታማኝ ባሪያ ና ወደ ጌታህ ደስታ ግባ » እያለ የሚጠራንን የጌታን ድምፅ ስንሰማ ለኛ እንዴት ያለ ታላቅ ቀን ይሆንልናል ። አሁንም እንኳን በሐሳባችንና በአድራጎታችን መንፈስ ቅዱስን ሳናሳዝን ቀርተን የሕሊና ወቀሳ በሌለብን ጊዜ ፤

« አንተ መልካም ባርያ » የሚል የመንፈስ ምስክርነት በውስጣችን ሲሰማን ምንኛ ደስ የሚያሰኝ ነው ። ሰውነታቸውን ለእግዚአብሔር ፈጽሞ ባስማስገዛት ለሳማቸውን የሚያጡ ስንት ናቸው ። በክርስቲያን ሕይወታቸው ፤ የመጠራጠርን ጥላ የሚጥልባቸው ድቅድቅ ያለ የኃጢአት ደመና ነው ። ክርስቶስ ብሏልና « የሚከተለኝ በጨለማ አይኖርም » ( ዮሐንስ ፰ ፲፪ ። )

እንደዚህ ያለው የኑሮ ግማሽ የሚያሳዝነው ፤ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለውን እርግጠኛነት የሚፈስበትን የእምነት ቦይ መድፈኑ ብቻ ሳይሆን ፤ በዳዊት እንደደረሰበት ሁሉ ፤ የጌታ ጠላቶች እንዲሳደቡና እንዲያቃልሉት ምቹ ጊዜ ይሰጣቸዋል ። ዓለማውያን የሆኑት ፤ በክርስቲያኖች ላይ ትንሽ ነቀፌታ ሲያገኙ ደስ ይላቸውና « እዩ ጉድ ክርስቲያኖች ነን እያሉ ይህን ይሠራሉ » ብለው ከመጠን በላይ እየጨማመሩ ይነቅፋሉ ፤ ግን ይህን በሚሉበት ጊዜ ፤ እነርሱ የሚያደርጉትን ኃጢአት ፤ ልዩ ልዩ ምክንያት በመስጠት ፤ ደበቅ ደበቅ ሲያደርጉ የራሳቸውን ጉድለትና በደል ያሳያሉ ።

አንተ ክርስቲያን እንደሆንህ ፤ የከበደብህንና የሚያበሳጭህን ኃጢአት አምዘግዝገህ እንድትጥል እለምንሃለሁ ። ( ዕብራውያን ፲፪ ፩ ። ) ታላቅ ዋጋ ያለውን በውስጥ የሚሰማንን የከበረ የመንፈስን ምስክርነትና በዓለም ፊት የምናሳየውን የራሳችንን ምስክርነት እንዳናጣ እንግዲህ ጣዖታዊውን ሥራ እንሻርና በርሱ ፈንታ ነዋሪ ሰላምን መስጠት የሚችል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እናንግሥበት ።



አንድ ጊዜ አንድ ሰውዬ በአንዲት ደሴት ሳለ አንድ ንሥር በሰማይ ሲከለፈለፍ በማየቱ ተደንቆ አንዱን ክንፉን በጥይት የተመታ መስሎት ፤ ትኩር ብሎ ይመለከተው ጀመር ። ነገር ግን ምንም የተኩስ ድምፅ ባለመስማቱ ነገሩ እንግዳ ሆኖበት ይገረም ነበር ። ወዲያውኑ ክንፎቹ ዝለውበት በደቂቃ ውስጥ እመሬት ዘፍ አለና በሰውዬው እግር ሥር ተንደፋደፎ ሞተ ።

ሰውዬው ጠጋ አለና ክንፎቹን እያገላበጠ ሲያይ አንድ ትንሽ አውሬ ሥጋውን በስቶ ልቡን ቦርቡሮ እንደበላ በወቀ ጊዜ የሞተበት ምሥጢር ገባው ። ይህ አሞራ እበላዋለሁ ብሎ ታናሹን አውሬ ከምድር ጠልፎት ይበር ነበር ። ነገር ግን በታላቁ አሞራ የተነጠቀው ታናሽ አውሬ ብርቱ ነበረና ተጣብቆ ቦርቡሮ በመብላት ታላቁን አሞራ ጥሎ ገደለው ።

የተወደድህ ክርስቲያን ኋላ ሆይ ፤ ቶሎ እደናቅፎ ከሚጥልህ ኃጢአት ጋር ተጣብቀህ አትኑር ። በአንድ ኃጢአት ላይ መጽናት ያለ ጊዜ መሞትን ሊያመጣ ይችላል ። ( ፩ኛ ቆሮንቶስ ፭ ፭ን ተመልከት ። )

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝህ አድርገህ ከወቅህ በኋላ ፤ ከኃጢአት የዳንህ እንደሆን ፤ « ድኛለሁ ወይስ አልዳንሁም » የሚል ጥርጥር ያመጣብህና እስክትመለስ ድረስ የመዳንህ ደስታ ያጠፋብሃል ።

## የደህንነት ፍጹም አስፈላጊነት ።

ቀደም ብለን ካደረግነውም ንግግር በኋላ እንኳ ፤ አንድ ሰው ወደ መንግሥተ ሰማያት እንዲገባ መዳን ያስፈልገው ይሆን ? እያሉ አንዳንድ ሰዎች ሳይ ደነቁ አይቀሩም ። አስፈላጊ መሆኑን እኔ አረጋግጥ ልሃለሁ ። ሰው ክርስቲያን መሆን የሚያስፈልገው በምን ምክንያት እንደሆን ፤ እዚህ በዝርዝር ለማሳየት አስፈላጊ አይደለም ። ክርስቲያናዊ ሕይወትን የሚኖርና በደስታ የተመላ የማይጠራጠር ክርስቲያን ፤ በእእምሮ ፤ በግብረ ገብነት ፤ በመንፈስ ፤ በማኅበራዊ ኑሮ ፤ በሰውነትም እንኳ ያለውን ጥቅም የማያውቅ አንድም ሰው አይገኝም ።

## ሰው ሁሉ ክርስቲያን መሆን ይገባዋል ።

አሁን እዚህ ላይ የምገልጸው ፡ ወደ ክርስቶስ መመለስና እሱን ማገልገል ፍጹም አስፈላጊ መሆኑን ነው ። ይህንንም ሳደርግ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲገቡ ለማስፈራራት ፤ በመሞከሬ እንደምወቀስ አውቃለሁ ። ይህን የጥበብና የዕውቀት ዘመን « በፍርሃት ወንጌል » ይደሰታል ብሎ ከማሰብ፤ ሌላ የበለጠ ነገር ቢያውቅ አይሻለውም ወይ እያሉ እንደሚያሙኝ ይሰማኛል ።



ያለ ክርስቶስ ብቻዋን ሁና የምትወዛወዘው ዓለም ፤ እርሱን በመጥላቷ የሚመጣባትን አስፈሪ ነገርና በመጥፎ ሁኔታ ላይ እንዳለች የሚያሳይ መልእክት ከመስጠት የበለጠ የማውቀው ምንም ነገር እንደሌለ ስማኝ፤ በግልጽ ልንገርህ ።

ገሃነመ እሳትን በመፍራት ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ እውነተኛ ክርስቲያን የሆነ አንድ ስንኳ ከቶ የለም እያሉ አንዳንድ ሰዎች ሲናገሩ ሰምቻለሁ ። ነገር ግን በፍርሃት ምክንያት ያመኑ ብዙ እውነተኞች ክርስቲያኖች አጋጥመውኛል ።

አንድ ሰው እንዲህ ሲል ተናገረ « በቤተ ክርስቲያናችን የሚሰብከው አብዛኛውን ስለ ገሃነመ እሳት ቢሆን ፤ ከቤቶቻችን ብዙዎቹ ይድኑ ነበር ። » ከአንድ ነገር ለመዳን እንደሚያስፈልግ የማያውቅ ሰው ፤ አዳኝ እንደሚያስፈልገው ፈጽሞ ሊያውቅ አይችልም ።

አንድ ወንጌላዊ « ምናልባት ዛሬ ማታ ትሞቱ ይሆናልና አሁን ክርስቶስን ተቀበሉ » ብሎ ለመስማት የተሰበሰቡትን ሲለምናቸው ያፌዙበታል ። « አሁኑኑ ክርስቶስን ተቀበሉ ነገ ትኖራላችሁና ፤ ለመሞት ሳይሆን ለመኖር ተዘጋጁ » ለምን አትለንም ይሉታል ። በበኩሌ ሁለቱም አስፈላጊ ናቸው እላለሁ ።

በዚህ በሠለጠነና ግድ የለሽ በሆነ ዓለም ውስጥ ፍርሃት በጣም አስፈላጊ ነው ። በቡር በፍጥነት ባጠገ

ባችን ሊያልፍ ሲል አቋርጦ ለመሄድ የምንፈራው ለምድነው ። አሰቃቂ በሽታ በያዘን ጊዜ ወደ ሐኪም የምንሮጠው ለምንድነው? ከስደንጋጭ አውሬ ሽሽተን የምናመልጠው ለምንድነው? ለዚህ መልሱ በጣም ቀላል ነው የምንፈራው ለሕይወታችን አስጊ ነገር እንደሚመጣ ስለምናውቅ ነው ።

ያለ ክርስቶስ ብሞት አልፈራም ፤ ኃጢአት ስለሚያመጣውም ቅጣት አልጨነቅም ፤ እያሉ መፎከር ድንቁርና ነው ።

አንድ የመጠጥ ሞቅታ የተሰማው ሰው «ፈጣኑ ባቡር እንደ ነፋስ እየበረረ በከተማው ሲያልፍ ሐዲዱ ላይ ቆሜ ገፍቼ ወደ ገደል ልጨምረው እችላለሁ» እያለ ሲፎከር ባልንጀሮቹ ሰምተው እንደዚህ ያለውን የቂል ሥራ አይሞክረውም ብለው ሰቁበት ። ነገር ግን በማግሥቱ ሰውነቱ በየስፍራው ተበታትኖ ሲያገኙ ፉከራውን ሊያጸድቅ መሞከሩን አወቁ ።

ይህ አደጋ ይመጣብኛል ብሎ አለመፍራቱ ሞትን አመጣበት እንጂ ሊያስቀር አልቻለም ። ወዳጄ ሆይ ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ገሃነመ እሳት እንዳለ ስለሚያረጋግጥ ላስጠነቅቅህ እወዳለሁ ። ያንተ አለማመን (መጠራጠር) እውነቱን ሊለውጥ አይችልም ወደዚያም ከመሄድ ሊያስቀርህ አይችልም ።



ሰይጣን የእግዚአብሔርን ጸጋና ምሕረት እንዳታይ እንደሚያሳውርህ እንዲሁ ገሃነመ እሳት የለም እያልህ እንዳትፈራ ሊያደርግህ ይችላል ።

## ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ናቸው ።

ኃጢአትህን ከራስህ የምታወርድበት ሌላ መንገድ የለምና የማይጠራጠር ክርስቲያን መሆን ያስፈልግሃል ። ፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፰ « ኃጢአት የለብንም ብንል እራሳችንን እናስታለን » ይላል ።

በአሁኑ ጊዜ ኃጢአት የሚባል ቃል እጅግ ተረስቷል በአንዳንድ በታማ ይኑር አይኑር የሚያውቀው የለም ። የሆነ ሁኖ በሮሜ ፫ ፳፫ « ሁሉ በድለዋል » የሚል ቃል ተጽፎ ይገኛል ። ዐመፅ ፤ መተላለፍ ፤ ክፋት ፤ መጠራጠር እነዚህ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኃጢአት ይባላሉ ። ዛሬ በዘመናዊው ዓለም ስሕተት ፤ ጥፋት ፤ ነውር ፤ እያሉ ለወጥ አድርገውታል ። « እነዚህ ጥቃቅን ናቸው ምንም አይደሉም » ለማለት ሰዎች ልዩ ልዩ ስም ቢያወጡላቸውም ለአባታቸው « ለኃጢአት» ቤተሰቦች መሆናቸው አልቀረም ። ስለዚህ ክርስቶስ እንደሚያድነን ካላረጋገጥን በኃጢአታችን እንሞታለን ። የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ካላመንን በኃጢአታችን እንደምንሞት እርሱ ራሱ በዮሐንስ ፰ ፳፬ ተናግሯል ። ይቅርታ የሚገኘው በማስተሠሪያ ነው ፤ ከኃጢአትም መንጻት የምንችለው እርሱ በቀራንዮ ባፈሰሰው ደሙ ነውና ክርሱ በስተቀር ይቅርታ የምናገኝበት ሌላ መንገድ የለም ። ( ፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፱ ተመልከት ። )

## ሕይወት ያለው በክርስቶስ ብቻ ነው ።

አንድ ጊዜ ወንጌላዊው ቆሞ ሲናገር አንድ ግድ የለሽ ሕንዳዊ ወጣት «የኃጢአት ሸክም የኃጢአት ሸክም ትላለህ ምንም የሚሰማኝ ነገር የለም ፤ ክብደቱስ ምን ያህል ነው ? ፩ ኪሎ ነው ወይስ ፴፮ ኪሎ » ብሎ ጠየቀው ።

ሰባኪውም «ክብደቱ አራት መቶ ኪሎ የሆነ ጭነት በሬሳ ላይ ብታደርግ ይሰማዋልን?» በማለት ቢጠይቀው ፤ ወጣቱ ፤ « ስለ ሞተ አይሰማውም » ሲል መለሰ ። ሰባኪው « እንግዲያውስ የኃጢአት ሸክም ያልከበዳትም ነፍስ እንደዚሁ የሞተች ናት » አለው ።

ይህም የሚያስደነግጥ ቃል በ፩ኛ ዮሐንስ ፭ ፲፪ ተጠቅሶ ይገኛል « ወልድ ያለው ሕይወት አለው ወልድ የሌለው <u>ሕይወት የለውም</u> » ይህ ጥቅስ ጳውሎስ በኤፌሶን ፪ ፩ ከተናገረው ጋር ተያይዞ ፤ ክርስቲያኖች ያልሆኑ ሰዎች በመንፈስ የሞቱ መሆናቸውን በዚህ የእውነት ቃል ያስረዳናል ።

እንግዲህ ለክርስቶስ ነገር ለምን ግድ እንደሌለህና ዘልብህም መጽሐፍ ቅዱስን ፤ ጸሎትን ፤ ሰዎችን ከኃጢአት ወደ ክርስቶስ ለመመለስ የማትወደው ለምን እንደሆነ ማወቅ ትችላለህ ።

የሠላሳ ሰዓት አሬሳና የሠላሳ ቀን አሬሳ ምንም ልዩነት እንደሌለው ፤ መንፈሳዊ ሞትም ከዚህ እስከዚህ ተብሎ የሚገመት ደረጃ የለውም ማለት ትንሽ ሞት



ትልቅ ሞት የለም ። ያማረ ልብስ ለብሶ እፁእዊ ክብር ያለው ሰው ፤ ያለ ክርስቶስ ከሆነ ፤ በኃጢአት ጭቃ እንደተዘፈቀና እንደተንቀሳቀሰ ልክ በመንፈስ እንደሞተ ምስኪን መሆኑ ነው ። « ወልድ የሌለው ሕይወት የለውም ። »

## መንገዱ ክርስቶስ ብቻ ነው ።

መንገዶች ሁሉ ወደ አክሱም እንደማያደርሱ ልዩ ልዩ መንገዶችም ወደ መንግሥተ ሰማያት አያደርሱም አይደርሱምም እያውቁ ።

ዛሬ ያልተማረው ተራ ሰው እውነተኛው የመንፈስ ጉዳና ጠፍቶት በመንፈሳዊ ጨለማ ይቅበዘበዛል ። ለራሱ ትክክል መስሎ የታየውን መንገድ ይዞ ቢሄድ ወደ ሰማያዊት አገር ይደርስ ይመስለዋል ።

አንድ ጊዜ አንድ ግድ የለሽ ወጣት « የልዩ ልዩ ቤተ ክርስቲያን አባል ብንሆን ምንም አይደለም የምንሠራው ወደ አንድ ቦታ እንድንደርስ ነውና » አለኝ ።

ለዚያው ስፍራ ( መንግሥተ ሰማያት ) ወይም እዚያው ሥፍራ ለመድረስ የምንሠራ አይደለንም ። ከብዙ ጊዜ በፊት በዓለም ያሉ መልክም መልክም ሥራዎች ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደማያደርሱኝ ተገንዝቤ ነው ። ይህንም የምልበት ፤ « ጽድቅ ሆኖ የሚቆጠርለት ለሚሠራ ሳይሆን ኃጢአተኛውን በሚያጸድቅ ለሚያምን » ስለሆነ ነው ። ( ሮሜ ፬ ፭ )

ክርስቶስ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት በምንም አኳኋን እንዳንጠራጠር መንገዱን አረጋግጦል ናል ። ሰዎች የደኅንነት መንገድ አይገባንም ብለው ምክንያት ሊፈጥሩ አይችሉም ።

ማንም ሰው ሊያስተውለው የሚችለውን ፣ ማንም ደግሞ ቢከራከርበት ሊለውጠው የማይችለውን የክርስቶስን ቃል አዳምጡ ። « መንገዱ እኔ ነኝ በእኔ በኩል ካልሆነ በስተቀር ማንም ወደ አብ አይመጣም ። » (ዮሐንስ ፲፬ ፮ ።) የጌታችን ጸሎት « አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር » ብሎ ስለሚጀምር አብ በሰማይ እንደሆነ እናምናለን ።

ስለዚህ ለመዳን ብንፈልግ ክርስቶስን መያዝ አለብን መንገዱ እርሱ ነውና ። የፈቀደንን ማድረግ ሳይ ሆን አንዱን መንገድ ብቻ መያዝ አለብን ይህን ካላደረ ግን መንግሥተ ሰማያትን አናገኝም ። አለመታዘዝና አለመስማማት ምንም ዋጋ የለውም ። ለግመኛነት የደ ኅንነትን በር ለዘላለም የሚዘጋብን አጥሬ መሣሪያ ነው ። በዚህ ዓለም ሳለን ልባችንን ዘግተን ክርስቶስን ብንቀ በል በኋላ መንግሥተ ሰማያት ይዘጋብናል ።

## የያንዳንዱ ኃላፊነት ።

« ስለዚህ እያንዳንዳችን ለእግዚአብሔር መ ልስ እንሰጣለን ። » (ሮሜ ፲፬ ፲፪ ።) ክርስቶስ ለሰ ኃጢ አት በመስቀል እንደሞተለት አምኖ የዳነው ክርስቲያን



ለሥራው ብቻ መልስ ይሰጣል ። ነገር ግን በክርስ ቶስ አምኖ ያልዳነ ሰው ለሥራው ብቻ ሳይሆን የክርስ ቶስን ደም ረግጦ ስለመሄዱ መልስ ይሰጣል ።

## ክርስቶስ ፈራጅ ይሆናል ።

በሐዋርያት ሥራ ፲፯ ፴፩ እንደተገለጸው ፣ መናፍቃን ( ያላመኑ ) በሚፈረድባቸው ቀን ዳኛው ራሱ ክርስቶስ ነው ። እያንዳንዱ ሰው ራሱ ለእግዚአብሔር መልስ በሚሰጥበት ጊዜ በምድር ሳለ የእግዚአብሔ ርን ልጅ ንቆ ያልተቀበለ ሰው ክርስቶስን ፈራጅ ሆኖ ያገኘዋልና ለዚያ ሰው ወዮለት ።

ሰው በጸጋ ወይም በፍርድ ክርስቶስን ለመ ገናኘት ምርጫ አለው ። ጌታችን « አላውቅሁምና ከኔ ራቁ » ብሎ ለመናገር ደስ ይለው አይመስለኝም ። ነገር ግን ያ ሰው በኃጢአት መኖርን መርጦ በራሱ ፈቃድ ሰውነቱን ለገሃነመ እሳት ሲያዘጋጅ ክርስቶስ ምን ያድርግ ? እውነተኛ ዳኛ ስለሆነ ፤ ሰውየውን በሕ ይወት ሥጋ ሳለ ወደ መረጠው ስፍራ ማሰናበት አለ በት ። ኃጢአቱን በእምነት በክርስቶስ ደም ያላጠበ ኃጢአተኛ እንዳይገባ መከልከሉ መንግሥተ ሰማያት አምነው ለገቡት የተገባ በመሆኑ ነው ።

## ዘላለማዊ ቅጣት ።

« ከእግዚአብሔር ፊትና ከሥልጣኑ ክብር ተለ ይተው ለዘላለም በሥቃይ ከመኖራቸው በስተቀር » የጠፉ ( የተኰነኑ ) ሰዎች ትክክለኛ ሁኔታቸው ምን እን

ደሆን ልነግርህ አልችልም ። ( ፪ኛ ተሰሎንቄ ፩ ፱ ። ) የቅጣት ደረጃ ሳይኖር አይቀርም ። እያንዳንዱ ሰው ነበልባል ዘልቆ የማይገባው አካል ስለሚኖረው በእሳት ውስጥ ለዘላለም እየተቃጠለ ይኖራል ።

« እግዚአብሔር ለጥቂት ኃጢአት ብሎ ሰውን እንዴት ወደ ዘላለም ሥቃይ ይሰዶዋል » ብለህ ትናገር ይሆናል ። በእውነት ኃጢአት መሥራት በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ እጅግ የሚያጸይፍ እስከ ሞትም የሚያደርስ ነው እንጂ ከቶ ቀላል ነገር አይደለም ። ነገር ግን ሰው ስለ ኃጢአቱ እንዳይሞት ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶዋልና ከሁሉ የበለጠ ኃጢአት ክርስቶስ ያዘጋጀውን ደህንነት አለመቀበል ነው ። ይህን ታላቅ መዳን ለመቀበል እምቢ የሚል ኃጢአተኛ የግድ ስለ ኃጢአቱ ይፈረድበታል ።

## የእግዚአብሔር ቸርነት ።

« እግዚአብሔር እጅግ በጣም ቸር ስለሆነ ማንንም አይኰንንም » ብለህ ትናገር ይሆናል ።እርግጥ ነው እኔም በዚህ እስማማለሁ እጅግ በጣም ቸር ነው ። ነገር ግን ከኃጢአትህ እንድትመለስና ምሕረቱን እንድትቀበል ሊለምንህና ሊማልልህ አልቀበልም ስትል ምን ያድርግህ ? ኃጢአታዊ ባሕርይህ ለእግዚአብሔር መንግሥት አይስማማምና ከነኃጢአትህ ወደ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ስንኳ ትሣቀያለህ እንጂ ደስታን አታገኝም ። ስለዚህ እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት ቢያስ



ገባ ኖሮ ቸርነት አይባልም ነበር ። አሁንም ደጋግሜ እነግርሃለሁ ። ኃጢአታዊ ባሕርይህ ለእግዚአብሔር መንግሥት አይስማማም ። ብትገባም ሥቃይ ይሆንብሃል ፡ ስለዚህ ነው እንቱን እዚያ በለማስገባቱ እግዚአብሔር እጅግ በጣም ቸር ነው ያልሁት ። « የሥጋ አሳብ የእግዚአብሔር ጠላት ነውና ለእግዚአብሔርም ሕግ አይገዛም ያንን አያችልምና ። » ( ሮሜ ፰ ፯ ። )

እግዚአብሔር ፤ ነፍሰ ገዳዮችን ፡ ሰካራሞችን ፡ አሰተኞችን ፤ ሌቦችን ፤ ቀንዘረኞችን ፤ ቁማርተኞችን ፡ እነዚህን የመሳሰሉትን ከዳኑት ጋር በአንድነት በመንግሥተ ሰማይ ለዘላለም እንዲኖሩ አለመፍቀዱ እጅግ በጣም ቸር ስለ ሆነ ነው ። በዚህ ዓይነት መንገድ ከሆነ መንግሥተ ሰማያት መንግሥተ ሰማያት አትሆንም ። በኃጢአት በተመሉ ታላላቅ ከተሞቻችን እንደሚገኙ ጐዳናዎች አደገኛ ሥፍራ ትሆናለች ። ዶክተር አይረንሳይድ የተባሉ « ገሃነመ እሳት እግዚአብሔር ያዘጋጀው ወህኒ ቤት ነው » ሲሉ ተናግረዋል ።

ሞት ሰውን ከከፋ ወደ ደግ ሊለውጥ አይችልም ፡ ይህን ማድረግ የሚችል በክርስቶስ ማመን ብቻ ነው ።

## ለመጥፋት ምንም ማድረግ አያሻም ።

ሥጋዊ ሰው የጠፋ ነውና ለመጥፋት ምንም ነገር ማድረግ አያስፈልገውም ።

ዮሐንስ ፫ ፲፰ « በርሱ ያመነ አይኰነንም የማያምንበት ግን አሁን የተኰነነ ነው በአንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም አላመነምና » ይላል ።

አንድ ጊዜ የተጨነቀ ወጣት መጣና « በአዳም ኃጢአት ምክንያት ሰው የሚጠፋው ለምን እንዲሆን አይገባኝም » አለኝ ። በዚያን ጊዜ ለመመስከርለት ዕድል አገኘሁ ። ክርስቶስ የመጣው የኃጢአትን ዕዳ ከፋሉ ከወረስነው የኃጢአት ባሕርይ ሊያድነን ብቻ ሳይሆን ራሳችንም ከምናደርገው ኃጢአት ጭምር ነው ። እንግዲህ አንድ ሰው ለመዳን አልፈልግም ብሎ ቢጠፋ እግዚአብሔር ኃላፊ ነውን ? እንዲህ ከሆነ የኃጢአትን ይቅርታና በወረስኸው ኃጢአታዊ ባሕርይ ላይ አሸናፊነትን ሲሰጥህ እምቢ ብትል በገዛ እጅህ ራስህን ጐዳህ እንጂ እግዚአብሔር የበደለህ አይደለም ።

አንተ ለመጥፋት ምንም ማድረግ አያስፈልግህም ። « ሁላችንም እንደ በግ ጠፋን ። » ( ኢሳይያስ ፶፫ ፮ )

ክርስቶስን መቀበል በጣም አስፈላጊ እንደሆነ በግልጽ የሚያስተምረውን የእግዚአብሔርን ቃል ፣ ለመቃወም የሚነሡ ክርክሮች በነፋስ ፊት እንዳለ ገለባ ናቸው ።

የእግዚአብሔር ቃል « ዳግመኛ መወለድ ይገባሃል » ይላል ። በዚህ ዘጋው ፤ እንዲህ ካለ ፡ እንደዚሁ ነው እኛም መታዘዝ አለብን ።



ከኃጢአት እንድንመለስ አያስገድደንም መመለስ ያለብን በራሳችን ፈቃድ ነው ። ወደው ያደረጉት ብቻ ነው የሚወደድና ደስ የሚያሰኝ ።

« ተመለሱ ተመለሱ . . . . ለምን ትሞታላችሁ»እያለ ሲጠራህ አትሰማውምን ?

## ምዕራፍ ፫ ።

## ክርስቲያን ፡ ለመሆን ።

አንድ ጊዜ ጓደኛዬ በፍጹም ልቡ በክርስቶስ ከማመኑ በፊት « ክርስቲያን ነኝ ብዬ ሁልጊዜ አስብ ነበር ። ምክንያቱም እስላም ያልሆነ ሁሉ ክርስቲያን ይመስለኝ ነበር » አለ ።

ሌላው ጓደኛዬም ከማመኑ በፊት በክርስቲያን ቤት ስላደገ ክርስቲያን የሆነ ይመስለው እንደነበረ ነገረኝ ።

ኢየሱስ ያሥራ ሁለት ዓመት ልጅ በነበረ ጊዜ ፤ ኢየሩሳሌም ደርሰው ሲመለሱ « አብሮአቸው ያለ መስሏቸው » ያንድ ቀን መንገድ እንደተጓዙ እንደ ዮሴፍና ማርያም ዛሬም ብዙዎቹ ክርስቲያኖች የሆኑ እየ መሰላቸው በመንፈሳዊ ረገድ የትም ሳይደርሱ ርቀው ሄደዋል ።

እንደዚህ ያሉ « በይመስለኛል » የሚሆኑ ነገሮች መሠረትና ጥልቀት የሌላቸው ናቸው ። አንድ ሰው ክርስቲያን መሆን የሚችለው እንዴት እንደሆነ በዚህ ምዕራፍ ለማሳየት ዋና ዓላማችን ነው ። ማናቸውም ሰው ማለት ሽማግሌ ፡ ወጣት ፡ የተማረ ፡ ያልተማረ ፡ ለደህንነት አስፈላጊ የሆነውን አንዱን ነገር ለማስተዋል እንዳያስቸግረው አገላለጹን በጣም ቀላል ለማድረግ እስበናል ።



በመጀመሪያ ክርስቲያን የማያሰኙትን ነገሮች ማሳየት የተሻለ ዘዴ መስሎ ይታየኛል ። እንቅፋቶችና ሐሰተኛ አሳቦች የሆኑትን ነገሮች እንደ ጦር ጠላቶች ከስመገድንና ከጠፉን በኋላ « ተፈላጊ ስለሆነው ስለ አንዱ ነገር » ብቻ እንደ ልብ ልንነጋገር እንችላለን ።

## ቤተ ክርስቲያን መሄድ አይደለም ።

አንድ ሰው ቤተ ክርስቲያን በሄደ ጊዜ ክርስቲያን መሆን የሚችል ሲሆን ፣ ብዙዎቹ የክርስትናን መንገድ ሳይዙ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ብቻ ክርስቲያኖች መባልን ሲወዱ መታየታቸው የሚያስገርም ነው ። « በምድር ላይ እውነተኛ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የኛ ብቻ ናት » አንዳንድ ወገኖች ( በታሪክም ሆነ በክህነት ሥራ እኛ ለመሆናችን ብዙ « ማስረጃ » አለን የሚሉ ) ክርስቲያን መሆንና ቤተ ክርስቲያን መሄድ አንድ ናቸው እያሉ ስለሚያስተምሩ ይህ አደገኛ የሆነ ሐሳብ እንዲስፋፋ አደረጉ ። ይህም መዳንን ምን እንደሆነ ለማወቅ በሚፈልጉ ሰዎች እእምሮ ውስጥ ጥርጥርን ይፈጥርና ለደህንነት አስፈላጊ ከሆነው ነገር ማርከ ይወስዳቸዋል ።

ዳሩ ግን እውነተኛ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ያንድ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን ይገባዋል ብዬ አምናለሁ ። ብርሃኑም በቤተ ክርስቲያኑ መስኮቶች ዘልቆ ማብራት አለበት ።

የእግዚአብሔርን ቃል አጥንተን ቤተ ክርስቲያኒቱ የክርስቶስ ራስ የሆነች የክርስቶስ አካል መሆኗና ክርስቲያኖች ሁሉ የአካሉ ብልቶች መሆናቸው ሲገባን ፤ ከዚያ ወዲያ የሕንፃ ቤተ ክርስቲያን አባሎች ቢሆኑም ባይሆኑ ፤ ቤተ ክርስቲያንን ( የክርስቶስ አካል ) ማዘውተር « ክርስቲያን እንደመሆን » ነው ለማለት ይቻላል ። ( ሮሜ ፲፪ ፬ — ፭ ። ፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፪ ፲፭ — ፲፱ ) ። በዚህ ጊዜ የቤተ ክርስቲያኒቱ እውነተኛ ራስ ከሆነው ከክርስቶስ ጋር አንድ እንሆናለን ።

## ዓመልን ማሻሻል አይደለም ።

ብዙውን ጊዜ የምንደናቀፈው ብትክትክ በሉ ሃሳቦቻችንና ምኞታችን ነው ። አሳባችንን ለዋውጠን መልካም ለመሆን እንሞክርና አንዱን ይዘን ሌላውን እንለቃለን ፤ ደግሞ በዚህ ሳይሆንልን ሲቀር ሌላውን እንጨብጣለን ፤ እንዲህ በማድረግ ክፉታችንን የምናቆም ይመስለናል ። ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ እስከ መጨረሻው የሚያደርሰን የለም ። እንዲሁም የሚሆንበት ምክንያት ግልጽ ነው ፤ ራሳችንን ለማሻሻል በኃይላችንስንጥር ነው ። ነገር ግን ክርስቲያኖች በሆንን ጊዜ በኛ ኃይል ሳይሆን በእግዚአብሔር ብቻ እንመካለን ። ከዚያ በኋላ ፍሬን ፍሬ ቢስ በሆነው ዛፋችን ላይ ማሰር ስንተው እርሱ ( እግዚአብሔር ) « ዛፉን መልካም ያደርገዋል ። »

ዓመልን ማሻሻል በሕይወታችን የታሪክ ገጽ የተጻፈውን መጥፎ ማስታወሻ ሊፍቅልን ከቶ አይችልም ። ሁለተኛ ከባንክ ገንዘብ አልበደርም ብሎ ሒሳብን መቁረጥ ባለፈው ያልተከፈለውን ዕዳ ሊያስቀር አይችልም ።

አንድ ሕይወቱ በክርስቶስ የተለወጠ ሰው እንዲህ ሲል ሰግሁት ፤ « ወንድሞቼ ፤ ዛሬ ማታ ዓመሉ የተሻሻለ ሌባና ሰካራም ሆኜ በፊታችሁ አልቆምም በጸጋ እንደዳነ ኃጢአተኛ እንጂ ። »

ዓመልን ማሻሻል ሰውን ክርስቲያን የሚያደርገው ከሆነ ፤ ሃይማኖታቸውን ገና ሳይለቁ ሥራቸውንና ጠባያቸውን ስላሻሻሉ ብዙ ቡዳይስቶችና እስላሞች ምን እንላለን ? ታዲያ ክርስቲያን ናቸውን ? አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ክርስቲያንም አረማዊም ሊሆን ይችላልን ? ጥቁር ከቶ ነጭ ነውን ? ነጭስ ጥቁር ?

የተወደድህ አንባቢ ሆይ ፤ ክርስቲያን መሆን ጠባይን መቀያየር አይደለም ። አዲስ ሕይወት መቀበል ማለት ነው ፤ ይህም እንዴት እንደሆነ በሚቀጥለው ገጽ ለማስረዳት እንሞክራለን ።

## ጊዜ የሚወስድ አይደለም ።

አንድ የታወቀ ነጋዴ ክርስቲያን በማኅበሩ ሰዎችን « ክርስቲያኖች » ለማድረግ ስለሚደረገው ሙከራ ሲናገር እንዲህ አለ ፤ « ልጆች ገና በሕፃንነታቸው በልማድ ብቻ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲሄዱ ያጣድፏ

ዋዋል ። ትልልቅ የሆኑት ደግሞ በእውነት ለግመናዋው የሚያረጋግጥ ነገር ሳይኖር የቤተ ክርስቲያን ማኅበርተኞች ይሆናሉ ።» ቀጥሎም ይህን የሚያስደንቅ ንግግር ተናገረ « ቀስ በቀስ ከጊዜ ብዛት እየገባቸው ክርስቲያኖች የሚሆኑ ይመስላቸዋል ። »

ክርስቲያን መሆን በአንዲት ደቂቃ የሚሆን ነው እንጂ ጊዜ የሚወስድ አይደለም ። ያልተፈጠረውን አዲሱን የክርስቶስን ሕይወት እግዚአብሔር በውስጣችን የሚተክልበት መለኮታዊ ሥራ ነው ። አዲስ ልደት ነው ፤ ልደትም ፤ ደርስ ወይም ሆኖ የሚያልፍ ነገር ነው እንጂ የሚደጋገም አይደለም ።

## ተላላፊ አይደለም ።

ደህንነት እንደተላላፊ በሽታ ክርስቲያን ከሆነው ክርስቲያን ወዳልሆነው በንክኪት የሚተላለፍ ቢሆን ኖሮ ማድረግ የሚያስፈልገው ያላመነውን ከመነው ጋር እያጠጋጉ የእግዚአብሔር ልጅ ማድረግ ብቻ ነበር ።

በዚህ አኳኋን አሳማን ወደ በግ ጃርትን ወደ ርግብ ለመለወጥ ይቻላል ማለት ነው ። ይሁዳ ትልቅ ዕድል አጋጥሞት ከጌታ ጋር ሦስት ዓመት ሲኖር ፤ በገዛጁ ከዳተኛ፤ሌባ ፤ ራሱን ገዳይ ሆነ ። ጥሩ ጥሩ ፍራፍሬዎች በሉበት መኻከል ያለ አንድ መጥፎ ፍሬ ወደዚያ ወደ መጥፎነቱ ያዘነብላል እንጂ ወደ መልካምነት አይለወጥም ።



ማንም ሰው ሌላውን ማዳን እንደማይችል በማቴዎስ ፳፭ የተጠቀሱት ጠባባት ( ብልሆች ) ደናግል በሰጡት መልስ ይታወቃል ። የሰነፎቹ ደናግል መብራት በጠፋ ጊዜ ከብልሆቹ ዘይት ለመኑ ። ነገር ግን ብልሆቹ « የለም ለናንተና ለኛ አይበቃም ወደሚሸጡት ሂዱና ግዙ » አሏቸው ።

እያንዳንዱ ሰው ለራሱ ደኅንነት በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር መሄድ አለበት ። አንድ ሰው ገንዘቡን በማስቱ ስም ሊያገኝ ይችላል ፤ ግን ደኅንነቱን በኢየሱስ ስም ማግኘት አለበት ። ( ሮሜ ፮ ፳፫ ። ዮሐንስ ፩ ፲፪ ። )

## በጥምቀት አይደለም ።

ጥምቀት በሰዎች የሚደረግ አፍአዊ ( የውጭ ) ሥርዓት ነው ። ሁለተኛ መወለድ ግን በመንፈስ ቅዱስ የሚደረግ ውስጣዊ ለውጥ ነው ። የፊተኛው ( ጥምቀት ) ለኋለኛው ( ሁለተኛ ልደት ) ምሳሌ ነው ።

ሰው የክርስቲያንን ሕይወት ሲጀምር የትንሣኤን ሕይወት ይጀምራል ። አሮጌው ሲሞት አዲስ ሕይወቱን ይጀምራል ። « በሞቱ ተጠመቅን . . . . ክርስቶስ ከሙታን እንደተነሣ እኛም ደግሞ በአዲስ ሕይወት እንሄድ ዘንድ ። » (ሮሜ ፮ ፩—፯ ተመልከት ።)

የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እኛን በክርስቶስ ሞት ማጥመቅና በዲስ ሕይወት እንድንኖር ማስነሣት ነው ። ይህ ነው ሁለተኛ መወለድ ። ይህ የሚሆነው ክርስቲያን

በሆነን ጊዜ ነው ። መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ሞት አጥምቆ ወደ አዲስ ሕይወት እንደሚያመጣን እንደዚሁ አጥማቂው ክርስቲያን ፣ ያ የሚጠመቀው ክርስቲያን ለኃጢአት ሞቶ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር እንደሚኖር ፣ ለዓለም ለመግለጽና የመንፈስን ሥራ በውኃ መስሎ ለማሳየት አማኙን ያጠምቀዋል ።

በውኃ ጥምቀት እድናለሁ ብሎ መታመን ሞኝነት ነው ። ራሷን መኸሬዩቱን ትቶ ስዕሏን አገባለሁ እንደሚል ሙሽራ ይቆጠራል ።

ይህ ስለ ጥምቀት አትቶ የሚነገርበት ስፍራ ስላልሆነ በአጠማመቁ ስለሚለያዩ፡ ሐሳቦች ልናገር አስፈላጊ መስሎ አይታየኝም ። ክርስቲያን መሆን የመንፈስ ቅዱስ ውስጣዊ ሥራ ከሆነ ፣ አንድን ዘንድ ውኃ መርጨት ፣ ማፍሰስ ፣ ወይም መዝፈቅ ( መንከር ) በፍጹም አስፈላጊ አይደለም ።

ይህም ብዙውን ጊዜ የምናየው ነው ። ተጠምቀው ክርስቶስን ገና ያላወቁትንና ከኃጢአታቸው ያልዳኑትን ብዙዎቹን አይተናል ። ባንድ በኩል ደግሞ ገና ሳይጠመቁ በቤተ ክርስቲያኖች « ከሞት ወደ ሕይወት የተሻገሩትን » በብዙ የሚቆጠሩትን አይተናል ። እኔም ራሴ ከመጠመቄ በፊት ክርስቲያን ሆኜ አራት ዓመት ድረስ ቆይቼ ነበርና አያሌ ሰዎች ወደ ክርስቶስ መርቼአለሁ ።







ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ ፤ እነሆም ፣ ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ ፤ እነሆም ፣ ድምፅ ከሰማያት መጥቶ — በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ ። ማቴ ፫ ፣ ፲፮ ፣ ፲፯ ።

## በአፍ ብቻ እምናለሁ ማለት አይደለም ።

አንድ ሰው በባንክ ያስቀመጠው አንዲት ሣንቲም እንኳ ሳይኖረው በባንክ ቤት ይታመን ይሆናል ። ወይም በበቡር አንድ ጊዜ እንኳ ሳይጓዝ በቡር አለ ብሎ ያምን ይሆናል ። ስልክ መኖሩን ሲያውቅ የማይሠራበት ይኖር ይሆናል ፤ እንዲሁም ሬዲዮ መኖሩን እያወቀ የማይጠቀምበት ይኖራል ።

እንደዚህም ሁሉ ሰዎች በአፋቸው ብቻ በእግዚአብሔር እያመኑ ወይም ስለ እግዚአብሔር እያወቁ በእውነት በፍጹም ልብ አይታመኑበትም እምነታቸውም በሕይወታቸው ምንም ሲጨመር አይታይም ።

አንዱን ሰው ክርስቲያን ነህ ወይ ብዬ በጠየቅሁ ቁጥር ስንት ጊዜ እንዲህ የሚል መልስ አገኛለሁ — « እንዴ ፤ በእግዚአብሔርና በክርስቶስ የማያምን አለ ? ምን ማለትህ ነው ? እኔም በእግዚአብሔርም እምናለሁ በክርስቶስም እምናለሁ ። »

ሰይጣናትም እንዲሁ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል ።

## ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው ?

እንግዲህ ክርስቲያንነት ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ፣ ዓመልን በማሻሻል ፣ ክርስቲያኖችን በመዳበስ ፣ በጥምቀት ወይም በአፍ ብቻ በእግዚአብሔር ማመን ካልሆነ ፡ ምንድነው ? ሰው ክርስቲያን የሚሆነው በምንድነው ? ( የሚል ሐሳብ ይመጣብሃል ። ) እንግዲያውስ



ከመጽሐፍ ቅዱስ በቀላሉ ልመልስልህ ።

በክርስቶስ ያመኑ ምዕመናን ሁሉ « ወንድሞች » « ምዕመናን » እንዲሁም « ደቀ መዛሙርት » ተብለው ይጠሩ ነበር ። ነገር ግን « ምዕመን » የሚያመለክተው በክርስቶስ የነበራቸውን ሕያው ሃይማኖት ነው ። ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ፤ የሚል እምነታቸው እንደሆንና ተሰቅሎ ሞቶ እንደገና ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ ያምኑ ነበር ።

በሐዋርያት ሥራ « ደቀ መዛሙርት ( ምዕመናን ) መጀመሪያ በአንጾክያ ክርስቲያኖች እንደተባሉ » እናነባለን ። እነዚህ ሁለቱ ቃላት በተመሳሳይነት እንድ ዓይነት ትርጉም እንዳላቸው እናያለን ። ይኸውልሃ ፡ በክርስቶስ ብቻ የሚያምን ክርስቲያን ይባላል ።

ክርስቲያን መሆን ምን ማለት እንደሆን ለማወቅ ብንፈልግ « አመን » የሚለውን ቃል እውነተኛ ትርጉሙን ማወቅ አለብን ።

በዮሐንስ ፫ ፡ ፴፮ « በወልድ ያመነ የዘላለም ሕይወት አለው » የሚል እናነባለን ። ሮሜ ፮ ፡ ፳፫ « የእግዚአብሔር ጸጋ ግን የዘላለም ሕይወት ነው በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን » ይላል ። በነዚህ ጥቅሶችና « ደቀ መዛሙርት ( አማኞች ) መጀመሪያ በአንጾክያ ክርስቲያኖች ተባሉ » በሚለው ጥቅስ ፤ ምዕመን ክርስቲያን እንደሆንና የዘላለም ሕይወት ለክርስቲያን በነፃ የሚሰጥ መሆኑን ልንረዳ እንችላለን ።

በውኃ ላይ መንሳፈፍ ስንማር ተዝናንተን ወኃው ይሸከመናል ብለን እንደምንተማመን እንዲሁ ለመዳን በክርስቶስ ክንድ ላይ አርፈን እንዝናናለን ፤ እንተማመናለን ፤ እንደ መድኃኒታችንና ጌታችን አድርገን እንቀበለዋለን ። እኛ ማድረግ የማንችለውን ለእርሱ እንለቅለታለን ። እኛ ለቀቀን ፤ ለእግዚአብሔር እንተውለታለን ።

ይህችን መጽሐፍ የሚያነቡ ፤(ያልዳኑት) ለማመን ነገ ተነገ ወዲያ እያሉ እንዳይዘገዩ ሳላሳስብ ይህን « ክርስቲያን ስለመሆን » የሚናገረውን ምዕራፍ ልዘጋ አልፈቅድም ።

አዳኝ ( መድህን ) እንደሚያስፈልግህ ታውቃለህ ፤ ኃጢአት በመሥራትህ የእግዚአብሔርን ክብር አጥተሃል ። ( ሮሜ ፫ ፳፫ ) መንግሥተ ሰማያት ቅድስት ስፍራ ስለሆነች የኃጢአትን ይቅርታ ሳታገኝ ከቶ ልትገባ ባት አትችልም ። ያለ ክርስቶስ ከሆንህ የጠፋህ ነህ ። ( ሉቃስ ፲፱ ፲ ) በክርስቶስ ካላመንህ አሁኑኑ የተኰነንህ ነህ ። (ዮሐንስ ፫ ፲፰ ፡ ፲፱ )

የሚያስፈልግህ አዳኝ እርሱ እንደሆነ ግን ታውቃለህ ። ከኃጢአት ሊያድንህ የሚችል እርሱ ብቻ ነው ። ( ዮሐንስ ፰ ፳፬ ) የይቅርታና የመንግሥተ ሰማይ መንገድ እርሱ ብቻ ነው ። ( ፩ ዮሐንስ ፭ ፲፪ ) በዮሐንስ ፲፬ ፮ እንዲህ ይላል ፦ « መንገዱ እኔ ነኝ ፤ ... በኔ በኩል ካልሆነ በቀር እንድም ወደ አብ የሚመጣ የለም ። »



የመወሰኛው ጊዜ አሁን ነው ፤ ራስህን ለማዳን የምታደርገው ምንም ነገር የለም ። ታዲያ ከኃጢአትህ ወይም በክርስቶስ እንዳታምን ከሚከለክልህ ነገር በቶሎ ተመልሰህ በርሱ ብቻ አትታመንምን ? ራስህንስ ለርሱ አታስረክብም ?

ደግሞም « አዎን ለማመን እፈልጋለሁ ግን እንዴት አድርጌ ነው ? በል እስቲ ንገረኝ ትላለህ ። » አዳምጥ ፤ እንዴት ስለሚለው ነገር አትጨነቅ ። ለመዳን ብትፈልግ እንዲህ በል « ክርስቶስ ሆይ እንዴት እንደሚዳንም ባላውቅ ለመዳን ፍጹም ፍላጎት አለኝ ። ሌላ የሚዳንበት መንገድ የለምና ሙሉ እምነቴን ባንተ ብቻ ጥዬ ከሁን ጀምሮ እንዳዳንኸኝ አምናለሁ ። እንተንም ጌታዬና አምላኬ አድርጌ እቀበልሃለሁ » ።

ስማኝ የተወደድህ አንባቢ ሆይ ፤ በቃሉ ሥልጣን ደህንነትን እንዳገኘህ ልታውቅ ትችላለህ ። « በጌታ በኢየሱስ እመን ትድናለህ ። » ( የሐዋርያት ሥራ ፲፮ ፴፩ )

## እንዴት እንደምናውቅ ወይም ፍጹም እርግጠኛነት ።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ ሌላ መከላከያ አያስፈልገውም ። በውስጡ ለማስተዋል የሚያስቸግሩ አንዳንድ ነገሮች ቢገኙበትም ብዙ ትምህርት ያላቸው ሰዎች በሚበቃ ገልጸዋቸዋል ። መጽሐፍ ቅዱስን ስታጠና ስሕተት ወይም ተቃራኒ የመሰለ ነገር ቢያጋጥምህ ፤ ይኸው ችግር አጋጥሞት መልሱን ያገኘ በአንድ ሥፍራ እንዳለ አስታውስ ። ከታመነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ብትጠይቅ አጥጋቢ መልስ ሊመጣልህ ይችላል ።

በእግዚአብሔር ቃል ላይ ጭቅጭቅና ክርክር የምታነሣ ፤ እንዲሁም በክርስቲያንነት የምትሳለቅ አንባቢ እንደሆንክ አንድ ነገር ብቻ እነግርሃለሁ ። ይኸውም እንዲህ ነው ፤ ክርስቶስን እንደ ግል መድኃኒት አድርጎ መቀበል ማለት ምን እንደሆነ ሲገባህ ለቃሉ በደስታ ትገዛለህ « ገና በመጠራጠር ላይ ሳለህ እንዴት ያለሁ ሞኝ ነበርሁ » እያልህ መደነቅና መገረም ይደርስብሃል ።

በሌላ አባባል « የዮሐንስ ወንጌል ፫ኛው ምዕራፍ ደህና አድርጎ ገብቶህ እንደሆነ በኦሪት ዘፍጥረት የሚገኘውን ፫ኛ ምዕራፍ ለማስተዋል ምንም አያስቸግርህም » ከዚያ ወዲያ አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት « መጽሐፍ



ቅዱስ እንደገና መጻፍ አለበት » አትልም ። « ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ተደግሞ መነበብ አለበት » ትላለህ እንጂ ።

ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን የሚነቅፉትና የሚያቃልሉት ትምህርቱን በለማስተዋል ወይም ጠማማ ትርጓሜ በመስጠት መሆኑን አውቄአለሁ ።

መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ ካልሆነ ክርስትናም እውነተኛ ሃይማኖት መሆኑ ቀርቶ ሰው ሠራሽ ሃይማኖት መሆኑ ነው ። እንደ ሃይማኖት መሆኑ ቀርቶ ከብዙዎቹ አንዱ መሆኑ ነው ። እንዲህ ከሆነ ክርስቶስ መድኅን መባሉ ቀርቶ መልካም ሰውና ታላቅ መምህር ብቻ መባሉ ነው ፤ ከዚህ ዓለምም በኋላ ስለሚሆነው ነገር እርግጠኛነት የለም ማለት ነው ። እንግዲያው « ይህ ትክክል ነው ይህ ስህተት ነው » እያለ የሚነግር ቃል ከሌለ ፤ ዓለም ሁሉ እንደልቡ ይፈንጥዝ ? መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ ካልሆነ ሰው በኃጢአት አልወደቀም አዳኝም አያስፈልገውም ይባላ ? እዩ ጉድ እንግዲህ በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ ተታለሉ ? በመመስገንም ፈንታ ይታዘንላቸዋ ።

ለእናንተ ደግሞ ክርስቶስን አውቃችሁት አንዳንድ ጊዜ ስለ ደህንነታችሁ ጥርጥር የሚገባችሁ በሚቀጥሉት አዲስ መስመሮች የምነግራችሁን በተለይም ከመጽሐፍ ቅዱስ የጠቀስኳቸውን ልብ አድርጋችሁ እንድትመለከቱ አሳስባችኋለሁ ። መንፈስ ቅዱስ ቃሉን እንደሚባርክላችሁና የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችሁን (ሁናችሁ እንደሆነ) በልባችሁ ውስጥ እንደሚመሰክርላችሁ እር

ግጠኛ ነኝ ። በዚያን ጊዜ ያለማመንታት « ለነፍሴ ነገሩ ሁሉ መልክም ነው » ስማለት ትችላላችሁ ። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የምታምኑ ከሆናችሁ እርግጠኛ ለመሆን መብት አላችሁ ።

## ምዕመናን ( አማኞች ) ሁሉ የጸደቁ ናቸው ።

ጽድቅ የሚያምን ኃጢአተኛ ጻድቅ የሚባልበት መለኮታዊ ሥራ ነው ። ክርስቶስ የኛ ምትክ ሆኖ የኃጢአታችንን ዕዳ ከፍሎልናል ። ( ኢሳይያስ ፶፫፡፮ ) በኛ ፈንታ ሞቶ እኛን ነፃ አድርጎናል ። አማኙ « የሚከሰስበት ምንም ነገር አለመኖሩን ለመስማት ፍርድ ቤት እንደመቅረብ ያህል ነው » በሐዋርያት ሥራ ፲፫ ፴፱ ስለ ኢየሱስ እንዲህ የሚል እናነባለን ። « ከኃጢአትም ሁሉ በሙሴ ሕግ ክርስዋ ትነጹ ዘንድ የማትችሉ በዚህ የሚያምን ሁሉ ይነጻል ። »

ሕግን ስለጣስን በሕግ ተፈርዶብናል ። ነገር ግን ከህደል ነጽተን ፍጹማን እንሆን ዘንድ በመፍቀሬ ሰብእ ( ሰውን ወዳጅ ) መድህናችን የሚያስደንቅ ደኅንነት ተዘጋጅቶልናል ። ይህም የሚሆነው ስለ ኃጢአት ቅጣት እኛ መቀበል የሚገባንን ለኛ ሲል በተቀበለልን በክርስቶስ በማመን ነው ። አንድ ሰባኪ « መጽደቅ ማለት ክርስቶስን ተቀብዬ እንደሆን እግዚአብሔር እኔን ኃጢአት እንዳልሠራሁ አድርጎ ይመለከተኛል ማለት ነው ። » አለ ።



## የኃጢአት ድምሳሴ ።

ያለፈው የክርስቲያኖች ኃጢአት ስለተሰረዘ የሚያስታውሰው የለም ። « ኃጢአታቸውንና በደላቸውን አላስብም ። » ( ዕብራውያን ፰ ፲፪ )

ኃጢአታችንን በተናዘዝን ጊዜ ይቅር ይለናልና እንደገና ያንኑ መልሶ መናዘዝ አያስፈልግም ።

አንድ ጊዜ ስለ ሠራው ኃጢአት በጣም የተጨነቀና ሰላምን ያጣ ነጋዴ አገኘሁ ። ስጠይቀው ስለ ሠራው ኃጢአት ማታ ማታ መላልሶ ይጸልይ እንደነበረ ነገረኝ ። ምንም መልስ ያላገኘ ሲመስለው ጊዜ « ይህን ሠራሁ ይህን ሠራሁ » እያለ የድሮውን ኃጢአቱን ሁሉ እየቆጠረ ለብዙ ወራት ይጸልይ ነበር ።

እንዲህ ያለው መናዘዝ ጥቅም የሌለው ነው ። በውነት ስለ ኃጢአቱ የሚያዝን ክርስቲያን ግን ምንም የሚሰማው ነገር ባይኖርም በተናዘዘ ጊዜ የኃጢአቱን ይቅርታ እንዳገኘ ያውቃል ። « በኃጢአታችን ብንናዘዝ እርሱ የታመነና ጻድቅ ነው ። ኃጢአታችንን ይቅር ይለን ዘንድ ከዓመፃም ሁሉ ያነጻን ዘንድ ። » ( ፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፱ )

ኃጢአትን መሥራት አይገባንም ። ለክርስቶስ በሙሉ የተገዛን ከሆንን ኃጢአት በፈቃድ አንሠራም ። ነገር ግን « ማንም ኃጢአት ቢሠራ ከአብ ዘንድ አማላጅ አለን ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቅ ለእኛ ብቻ አይደለም ለዓለም ሁሉ ኃጢአት እንጂ ። » ( ፩ ዮሐንስ ፪ ፡ ፩፡፪ )

ኃጢአታችንን በተናዘዝን ጊዜ ፥ ክርስቶስ « አባት ሆይ ፡ በቀራንዮ ደሜን ያፈሰስሁለት ይኸው ። በኔ መሥዋዕታዊ ሞት ለኃጢአቱ ማስወገጃ እንዳዘጋጀንለት አውቆ ከነኃጢአቱ ወደኔ መጥቷል ። በሚመጣው ታላቅ ቀን እንደማይርገው ሁሉ በክብርህ ፊት ነውር የሌለበት ሆኖ አሁንም አቀርበዋለሁ » ብሎ እንደሚያቀርበን ነው ። ( ይሁዳ ቁ. ፳፬ን ተመልከት ) አሁን ይገባሃል ? እንዳያመልጥህ ይህን ድንቅ እውነት ብትጨብጥ በእርሱ ( በክርስቶስ ) የተጠበቅህ መሆንህን እንድታውቅ ያደርግሃል ።

ቀጥሎ ያሉት ቃላት እግዚአብሔር ኃጢአትን እንዴት እንደሚያስወግድ ይገልጹልናል ። እነዚህም ይቅርታ ፡ መፋቅ ፣ ማንጻት ፣ አለማስታወስ ፣ ኃጢአታችንን በሥጋው በእንጨት ላይ ተሸከመ ፥ ስለእኛ ኃጢአት አደረገው ፡ ለኃጢአታችን ሞተ ፥ ኃጢአታችንን በደሙ አጠበ ፥ ስለ ብዙዎች ኃጢአት ይቅርታ ደሙ ፈሰሰ ። ብዙ ናቸው ሌሎችም አሉ ።

## የክርስቲያን ፍርድ ።

መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቲያን ላይ ስለሚመጡት ሁለት ፍርዶች ይናገራል ። ክርስቲያን የሆኑና ያልሆኑ መልስ ለመስጠት በአንድነት የሚጠሩበት ጠቅላላ ፍርድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በየትም ሥፍራ አይገኝም ። በዮሐንስ ራዕይ ም. ፳ የተጠቀሰው ታላቁ ነጭ ዙፋን በሥራቸው ተፈርዶባቸው በዘላለም ጨለማ ለሚጣሉ ላልዳኑ ሰዎች ብቻ ነው ።



በ፪ኛ ቆሮ. ፭ ፡ ፲ « ሁላችንም በክርስቶስ ወንበር ፊት መገለጥ ይገባናል » የሚል እናነባለን ። ዶክተር ፔትንግል የሚባሉ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ « የክርስቶስ ወንበር የጨዋታ ተወዳዳሪዎች በሸነፉ ጊዜ ሽልማት ለመቀበል እንደሚቆሙበት ሥፍራ ያለ ፤ አማኞች ዋጋቸውን ለመቀበል የሚቆሙበት ሥፍራ ነው » ። እዚህ በተጠቀሰው ጥቅስ ላይ ጳውሎስ የሚናገረው ስለ ክርስቲያኖች ብቻ ነው ። በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ለሠሩት ሥራ ሽልማታቸውን ለመውሰድ በፍርድ ዙፋን ፊት የሚቀርቡ አማኞች ብቻ ናቸው ። ዋጋቸውም እንደሥራቸው መጠን ነው ። አንዳንዶቹ ጥቂት ወይም ከነጭራሹ ምንም ዋጋ ሳያገኙ ሲቀሩ አንዳንዶቹ ደግሞ ከሌሎቹ የበለጠ ዋጋ እንደሚያገኙ እርግጥ ነው ።

በደህንነትና በዋጋ መከከል ልዩነት እንዳለ ለይቼ ልናገር እወዳለሁ ። ደህንነትን የምናገኘው ክርስቶስ በቀራንዮ በፈጸመው ሥራ ነው ። እኛም ይህንን በተቀበልን ጊዜ የመንግሥተ ሰማያት በር ይከፈትልናል ። ክርስቲያኖች ሆነን በምድር ላይ ስለሠራነው ሥራ ዋጋ የምንቀበለው ክርስቶስ ሲመጣ ነው ። ይህም ማለት በክርስቶስ በማመናችን ደህንነትን ስንቀበል በክርስቲያናዊ ሥራችን ዋጋ እንቀበላለን ማለት ነው ።

የክርስቲያን ኃጢአትስ ? በሠራው ኃጢአት ፍርድ የለበትም ? አዎን በእርግጥ አለ ። ግን (ከመን በኋላ) ስለሥራው ስለአገልግሎቱም የሚፈረድበት ወደፊት ሲሆን ፥ የኃጢአቱ ፍርድ ያለፈ ነው ። የፊተኛው

የሚሆነው በክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት ሲሆን የኋለኛው የተፈጸመው በመጀመሪያ መምጣቱ ነው ። እግዚአብሔር አብ በቀራንዮ መስቀል በልጁ ላይ ኃጢአታችንን አኑሮ ፈረደበት ። (ኢሳ. ፶፫ ፥ ፮ ። ፩ጴጥ. ፪ ፥ ፳፬ ።) እርሱ ክርስቶስ ስለኛ ኃጢአት ሆነ ። (፪ቆሮ. ፭ ፥ ፳፩ ።) ስለኛ ሞተ ። (ሮሜ ፭ ፥ ፰) « ስለኛ » ማለት በኛ ፈንታ ማለት ነው ። ስለዚህ የኛ ፍርድ በርሱ ተፈጸመ ። እንግዲህ ዋናው ነገር እኛ ኃጢአትን ምን እንደምናደርገው ሳይሆን ክርስቶስ ምን እንዳደረገውና እኛ ደግሞ ክርስቶስን ምን እንደምናደርገው ነው ።

እውነተኛው ክርስቲያን በኃጢአት ፈጽሞ አይፈረድበትም « በራሱ ፈንታ በሞተው ውስጥ ሆኖ በእምነት ቅጣቱን ተቀብሏል ። »

ምዕመን ስለዳነበት ማረጋገጫ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚያገኘው በዮሐ. ፭ ፥ ፳፬ የተጻፈው የክርስቶስ ቃል ኃይለ ቃል ያለው ነው ። ይኸውም እንዲህ ነው « እውነት እውነት እላችኋለሁ ነገሬን የሚሰማ በላከኝም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው ወደ ፍርድም አይሄድም ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ። እነዚህ ሦስት ነገሮች ግልጽ ናቸው ። « በላከኝም » በእውነት የሚያምን ያለጥርጥር « የዘላለም ሕይወት አለው » « ወደ ፍርድም አይሄድም » « ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ » ።



አስቲ አስብ ፤ ወደ ፍርድ አንሄድም ፡ እንዴት የድንቅ ድንቅ ነው ፤ በፍጹም አንኰነንም ማለት ነው ፤ « ኩነኔ » ተብሎ የተተረጐመው የግሪክ ቃል « ክረሰስ » በዕብ. ፱ ፥ ፳፯ ከሚገኘው ጋር አንድ ነው ። « ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከርሱ በኋላም ፍርድ (ክረሰስ) «እንደተመደበባቸው » ይህ ጥቅስ ፤ ዕብ. ፱ ፥ ፳፯ የሚናገረው ስላልዳኑት ኃጢአተኞች ፍርድ ነው ።

ክርስቶስ ወደ ፍርድ እንደማንሄድ ይናገራልና ይህን እውነት አጥብቀህ ያዝ ፡ ቃሉም አይታበልም ። ይህን አሸናፊ እውነት ጨብጠህ ፤ ፍርድ እንደሌለብህና ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሻገርህ ብታውቅ ጥርጥርን ሁሉ ለነፍስ ጥለህ ያዳነህን « ክርስቶስ ሆይ አመሰግንሃለሁ ፤ አምናለሁ ፤ አውቃለሁ » እያልህ በልብህ ምስጋና እንደምታቀርብ የማይጠረጠር ነው ።

## አማኞች አሁኑኑ የዘላለም ሕይወት አላቸው ።

ዘላለማዊ ኑሮና ዘላለማዊ ሕይወት አንድ ዓይነት ነገር አይደሉም ። ሰውየው ክርስቲያን ቢሆንም ባይሆንም የሰው ነፍስ ለዘላለም ትኖራለች ። ክርስቲያኖች ያልሆኑ ሁሉ ከመኖር ወደአለመኖር ይለወጡና ተነው በነነው ይቀራሉ እያሉ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያጣምሙ አሉ ፡ ነገር ግን ሐሳባቸውን የሚያግዝ ከመጽሐፍ ቅዱስ ከቶ አላገኝሁም ። )

የጻድቁት « ለዘላለም ከጌታ ጋር » ሲኖሩ ያል ጻደቁት ከእግዚአብሔር ተለይተው ለዘላለም በገሃነመ እሳት ይኖራሉ ። ያልዳኑ ሰዎች ሁለተኛ ያልተወለደ በሕርያቸው በእግዚአብሔር ፊቃድ ላይ ሁልጊዜ ስለሚ ያምፁ መንግሥተ ሰማያት ቢገቡም አይደሰቱም ። መን ግሥተ ሰማያት ከገሃነም ይልቅ የባሰ ይሆንባቸዋል ። እግዚአብሔርም ወደ መንግሥተ ሰማያት እንዲገቡ ከሚያ ስገድዳቸው በኃጢአታቸው ወደ ገሃነም እንዲሄዱ ቢፈ ቅድላቸው ይሻላል ።

እኛ ክርስቲያኖች የዘላለምን ሕይወት ለመቀ በል መንግሥተ ሰማያት እስክንገባ ድረስ መጠበቅ የለብ ንም ። አሁኑኑ የዘላለምን ሕይወት ጨብጠናል ። « ይህ ችን ነገር ጻፍሁላችሁ አላንተ በእግዚአብሔር ልጅ ስም የመናችሁ ታውቁ ዘንድ የዘላለም ይሕወት እንዳላ ችሁ ። » (፩ዮሐ. ፭ ፡ ፲፫) « ነገሬን የሚሰማ በሰደደኝም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው ። » (ዮሐ. ፭ ፡ ፳፬ ።) « « እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት እንደሰጠን ይህችም ሕይወት በልጁ አለች ወልድ ያለው ሕይወት አለው ። » (፩ ዮሐ ፭ ፡ ፲፩ ፲፪ ።) ስለዚህ ክርስቶስን ከያዝን ሕይወት አለን ። እነዚህ ሁለቱ የማይነጣጠሉ ናቸው ። እኛ የአ ካሉ የቤተ ክርስቲያን ብልቶች በመሆን ከርሱ ጋር አንድ ነን ። የቤተ ክርስቲያኒቱም ራስ እርሱ ነው ።

ወዳጄ ሆይ ፡ የዘላለም ሕይወት ዘላለማዊ ነው ። ዛሬ ድነን ነገ እንጠፋ ይሆን እያልን መፍራት



አያስፈልገንም ። አንድ ሰው ግሩም የሆን ነገር ተናገረ « ራሳችን ከውኃ በላይ ከሆነ ፈጽሞ አንሰምጥም ። »

## የክርስቶስ ጠባቂ ኃይል ።

ትምክህታችን በራሳችን ሳይሆን እንዳንወድቅ ኃይል ሁሉ ባለው በሚጠብቀን በክርስቶስ ነው ። (ይሁዳ ፳፬) ኤፍ ኢ. ማርሽ የተባሉ ፍሬያማ በሆነ ሕይወት ረጅም ዘመን ኖረው ሊሞቱ ሲሉ « ክርስቶስ በኃይማኖት ስለ ጠበቀኝ ኃይማኖትን ጠብቂአለሁ » አሉ ።

በ፩ኛ ጴጥሮስ ፩ ፡ ፫—፭ እንዲህ የሚል ማረጋገጫ ቃል ተሰጥቶናል ። « ይህም ርስት በመጨ ረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ ለናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል ። » ርስታችን በመንግሥተ ሰማያት ለእኛ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን እኛም ለርሱ የተጠበቅን ነን ። መንግሥተ ሰማያትን የሚያዘጋጅልን አምላክ እኛንም ለ መንግሥተ ሰማያት ያዘጋጀናል ። ልባችንን በዚህኛው ዓለም እንደ ከፈትንለት እርሱም መንግሥተ ሰማያት በ ወዲያኛው ይከፍትልናል ። ምንም እንኳን አልፎ አልፎ በድንጊያው ( ክርስቶስ ) ላይ ብንወድቅ ( ብንበድለው ) በጸጋው ከድንጊያው ( ክርስቶስ ) ተገሸራተን ከቶ አን ወድቅም ። ከጁ የሚነጥቀን የለም ። )

## የመንፈስ ቅዱስ ማኅተም ።

ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ ። (ኤፌ. ፬ : ፴ ።) « የቤዛ[ችን] » የሚለው ክርስቶስ ለርሱ የሆኑትን ለመውሰድ ሁለተኛ ጊዜ የሚመጣበትን ቀን ነው ። በዚያን ቀን እርሱን በአየር ለመቀበል እንነጠቃለን ። « እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን ። » (፩ ተሰ. ፬ : ፲፯ ።)

እስከ ቤዛ ቀን ፥ ወይም እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ድረስ ስለታተምን ከዚያም በኋላ ሁልጊዜ ከጌታ ጋር ስለምንኖር የተስፋችንን ምስክርነት ጠብቀን ያለማመንታት እምነታችንን አጥብቀን ስንይዝ ቃሉን በሚጠብቅ በእርሱ ኃይል ብቻ ዕረፍትን ለማግኘት እንችላለን ። ለኛ የሰጠውን ቃል ስለሚጠብቅ ክብሩ አይዘበም ።

ዋጋው ይህን ያህላል ተብሎ የማይገመት ወርቅ ባንክ ቤት ለማስቀመጥ ብንሄድና ባንክ ቤቱ ... ትልቁ የገንዘብ ማስቀመጫ እስኪዘጋጅ በሚ... ወር እስከዚህ ጊዜ ድረስ ወርቃችሁን በዚህ ... እናስቀምጥላችኋለን » የሚል ማረጋገጫ ቃሉን ሰጥቶን ይጠፋብናል ብለን አንፈራም ። እንደዚሁም ... ክርስቶስ ተመልሶ ከእርሱ ጋር ለዘላለም ወደምንኖርበት ታላቅ ስፍራ እስክንነጠቅ ድረስ በመንፈስ ቅዱስ ታትመናል ።

እንግዲህ ሊዋሽ በማይችል አምላክ የተሰጡንን እነዚህን የማይሻሩ የተስፋ ቃሎች ከያዝን « ምንም የለብንም በእርሱ ድነናል » ብለን ከማመን በስተቀር ሌላ ምን የምናደርገው ነገር አለን ?



በእግዚአብሔር ፊት ከጸደቅን ፥ ኃጢአታችንን ተደምስሶ ከተረሳ ፥ የሚጠብቀን ኩነኔና ፍርድ ከሌለብን ፤ ዘላለማዊ ሕይወት ዘላለማዊ ሐብታችን ከሆነ ፤ ሁሉን ከሚችል ከክርስቶስ እጅ የሚነጥቀን ከሌለ ፥ በመንፈስ ቅዱስ ከታተምን ፤ እንዴት ያለ የማይጠረጠር የእርግጠኛነት መሠረት ተሰጠን ። እነዚህ የእውነት ነገሮች በግርማና በታላቅነት በፊታችን እየተደቀኑ ፤ የሚመጣብንን ጥርጥር ሁሉ በእሳት ነበልባል ፊት እንዳለ የበረዶ ክምር እያሟሟሹና እያቀለጡ ድራሹን ያጠፉታል ።

ይህ ሁሉ እንደሆነ ሲታሰበን ዓይነ ልቡናችንን ወደ ሰማይ አቅንተን የማያቋርጥ የምስጋና መሥዋዕት እናቀርባለን ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞተልኝ ፥
ማንም አይፈርድብኝም ።
ከበቱም ሲለምንልኝ ፤
ጸጋው አይቀርብኝም ።
ጠበቃዬም ሲሆንልኝ ፥
ማን ሊከሰኝ ይችላል ፥
በከሃሊ እጁም ሲይዘኝ ፥
ከርሱ ማን ይነጥቀኛል ።

ምዕራፍ ፰

## የማይጠራጠረው ክርስቲያን ሕይወት ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ አድርገን በእምነት በተቀበልን ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንሆንና እግዚአብሔር አብ የተቀደሰ ባሕርይ ያስድርብናል ። አዲስ ፍጥረት ነን ። አሮጌው ሥራ ፈጽሞ ይሄድና ሁሉ ይታደሳል ። ( ፪ቆሮ. ፭ : ፲፯ ። )

## የመልካም ሥራ ኑሮ ።

ውስጣዊው አዲስ ሕይወት በአፍአዊ አዲስ ሕይወት ይገለጣል ። መልካም ሥራችን የማያይነን ቢሆንም ሰማያዊ አባታችን መልካም ሥራ በመሥራት እንድንኖር አዘጋጅቶ አቅዶልናል ። « እኛ ፍጥረቶቹ ነንና መልካም ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን ። » ( ኤፌ ፪ : ፲ ። )

እኛ ክርስቲያኖች የሆንነው በቅድስና እንድ ንኖር መሆኑን የላይኛው ጥቅስ በግልጽ ይናገራል ። መተንፈስ የተፈጥሮ እንደሆነ ለክርስቶስ መኖርም የተ ፈጥሮ ይሆናል ። ይግሞግም ሽታ የጽጌ ረዳ ባሕርይ እን ደሆነ መልካም ሥራ የባሕርያችን ይሆናል ። የማይጠ ራጠረው ክርስቲያን ከመነ በኋላም አሮጌውና ክፉው



ባሕርይ እንደማይለቀው እውነት ቢሆንም በውስጡ ያለ ው አዲሱ ሰው ያይላል ። እግዚአብሔር ከቅማችን በላ ይ የሆነ እንደ ፈተና እንኳን እንዳይመጣብን አድር ጓል ። ( ፩ቆሮ. ፲ : ፲፫ ። )

ትክክለኛ ኑሮ መኖርንና በኃጢአት ላይ ድል ን የምናገኘው በውስጥ ያለው አዲሱ ሕይወት እንዲያድ ግና ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ እንደተናገረው « ምንም ክፉ እንድናደርግ የሚስበን ሓሳብ ገና በውስጣችን ቢኖር ፥ መልካሙን እንድናደርግ የሚስበን ሓሳብ ከእርሱ የበረታ ነው ። »

ከሰብአዊ አቅም በላይ የሆነው በውስጣችን የሚኖር የክርስቶስ ኃይል ፥ ልንኖር የማንችለውን ኑሮ እንድንኖር ያደርጋል ።

ሰባት ዓመት ሆኖት መራመድ ፥ መነጋገር ፥ ማየት ወይም መስማት የማይችል አንድ ልጅ ነበር ሲባል ሰማሁ ። ሕይወትም ቢኖረው መኖር አይባልም ። እን ዲህ ያለ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር እግዚአብሔር አይበ ለው ።

እውነትን በእርግጥ ብናውቅ በእውነት ነፃ እንሆናለን ። ሰነፉም የነበረው ሰካራም አይሆንም ። እል ም ያለ ጠጪ የነበረው ጭምትና ደንበኛ ያገር ሠራዊ ይሆ

ናል ፡ ተራጋሚና ዓለኛ የነበረው የእግዚአብሔርን ምስጋና ብቻ የሚያወራ ይሆናል ። እምነተ ቢሱ እምነት ያለው ይሆናል ። ሌባው ወደ ታማኝነት ይለወጣል ። አእምሮ ቢስና ቀበጥ ዘፈን ወዳጅ የነበረችው ልጃገረድ የመስቀል ወታደር ሆና በደስታና በተድላ የምትኖር ትሆናለች ። ርኩሰትና ምናምንነት ወደ ንጽሕናና ወደ ቅድስና ይለወጣሉ ። ጥላቻ ወደ ፍቅር ፤ እታላይነት ወደ ደግነት ፤ ዓለማዊነት ወደ መንፈሳዊነት ይለወጣል ። ኃጢአትን የመውደድ ጣዖታት ይሰበበሩና በልብ ውስጥ ክርስቶስ ራሱ ይነግሣል ።

ክርስቲያንነት ሕይወት ነው ። ክርስቶስን በዙሪያችን ሳሉ የምናሳይበት በውስጥ ያለ የክርስቶስ ሕይወት ማለት ነው ። አዲስ ሕይወት ከለ አዲስ መኖር አለ ። « ትክክለኛ ኑሮ እንድንኖር ላያደርገን የትክክለኛ መኖርን ስሜት የሚሰጥን ሃይማኖት የክርስቲያን ሃይማኖት አይደለም » ተብሏል ።

## በሐዘን ፊት ።

የማይጠራጠረው ክርስቲያን ሕይወት ብዙና ልዩ ልዩ የሆኑ ነገሮች ያሉበት ነው ። ደስታና ሐዘን ይገጥሙታል ። አንዳንድ ጊዜ ከፃር ጥልቀት ወደ ተድላ ጫና ይወጣል ። በማግሥቱም ያልታሰበ ሐዘን ሲደርስበት በብቸኝነት በልቅሶ ሸለቆ ሲጓዝ ይገኝ ይሆናል ።



የማይገፋ መስሎ በሚታይ ጭንቀት እንኳ መንፈስ አለሁህ የሚል መዓዛውን ያሸተዋል ። ማንኛውም ነገር እየባሰ የሚሄድ መስሎ ቢታየው እንኳ ሁሉም ነገር ደህና እንደሆነ ያውቃል ። ሰይጣን የዚህ ዘመን ገዥ ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር ደግሞ የሕይወት እሳዛኝ የሆኑትን ነገሮች ለክርስቲያኑ የበረከት ተራሮች ለማድረግ ችሎታ ያለውና የሚያደርግ « የበላይ ገዥ » መሆኑን ያምራል ። « እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን ። ( ሮሜ ፰ ፣ ፳፰ ። ) »

## ሰዎች እንዲድኑ መጣር ።

በክርስትና ጉዞአችን ከምናገኛቸው እድሎች ሁሉ የሚበልጠው ሰዎችን ለክርስቶስ መማረክ ነው ። የጠፉት እንዲድኑ መጣር ከሁሉ የበለጠ ባሕርያዊ ነገር መሆን አለበት ።

በጳውሎስ ሕይወት እንደዚሁ ነበር ። ወደ ሮሜ በጻፈው መልእክቱ ፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ከገኘው ከእግዚአብሔር ፍቅር የሚለየው ምንም ነገር እንደሌለ በኃይለ ቃል ይናገራል ። ( ሮሜ ፰ ፣ ፴፭ — ፴፱ ) ። አማኙ በክርስቶስ የሚያገኘውን መጠበቅ ( የደኅንነት ) ጳውሎስ አረጋግጦ ሲናገር በደስታ ስውነታችንን ቀስቅሶ ከተቀመጥንበት እንደዔት ብድግ ያደርገናል ፤ ጳውሎስ ግን እን

ደዚሁ መጻንን አውቶ በማይነገር ደስታ ልቡ ሲፈነ ድቅ ፤ ከክርስቶስ ውጭ ሆነው ለጠፉት በጣም ያዝን ነበር ። ላልዳኑት ሰዎች ከማዘኑ የተነሣ « ብዙ ሐዘን የማ ያቋርጥም ጭንቀት በልቤ አለብኝ ስል በክርስቶስ ሆኜ እውነትን እናገራለሁ ፤ አልዋሽምም ፤ ሕሊናዬም በመን ፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል ። በሥጋ ዘመዶቼ ስለሆኑ ስለወንድሞቼ ከክርስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንድሆን እጸልይ ነበርና » እያለ ይደነፍቅ ( ያለቅስ ) ነበር ። ( ሮሜ ፱፥፩—፫። )

ክርስቲያን ወንድሜ ሆይ ፡ ስላልዳኑት ጓደኞ ቻችንና ወዳጆቻችን ከመጨነቅ በስተቀር ምን ለማድ ረግ እንችላለን ? የደህንነታችን ፍጹም እርግጠኛነት ከአለን ፤ እኛም እንደ ጳውሎስ ባለማቋረጥ ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ሳናርፍ እንደምንሞክር እርግ ጠኛ ነኝ ።

ስለ ጌታችንና ስለ አዳኝነቱ ከሰዎች ጋር ለመ ነጋገር ሁልጊዜ ቀላል አይሆንም ። የነሃነም ኃይሎች ሁሉ የሚጐለብቱብንና በከንፈራችን እንደ ማኅተም የተ መረገብን የሚመስለን ጊዜ ይኖራል ። አንድ ሰው « አፋ ችን እንደ በረዶ ይቀዘቅዝብናል » ነገር ግን « የክርስቶ ስ ፍቅር ያስገድደናል » ብለን ለመናገር እንችላለን ሲል ተናገረ ። ከክርስቶስ ውጭ የሆኑት የጠፉ ናቸው ። እግዚአብሔርም እነርሱን የሚያድንበት ሌላ መንገድ የለ



ውም እኛ ካልመሰከርንላቸው በተቀር ለመዳን ከቶ የማ ይችሉ ነፍሳት ( ሰዎች ) እንዳሉ እምናለሁ ። እግዚአብ ሔርም ሰዎች እንዲድኑ ኃላፊነቱን እውነተኛ ክርስቲያን በሆነ ሁሉ ላይ ጥሎታል ።

ሙዲ የተባሉ ታላቅ መምህር የሕይወታቸው ሕግ አድርገውት ስለ ክርስቶስ ለሰው ሳይመሰክሩ አይ ውሉም ነበር ይባላል ።

እግዚአብሔር « ለሚታዘዙኝ መንፈስ ቅዱ ስን እሰጣቸዋለሁ » ሲል ተስፋ የሰጠው ፤ በሌላው ነገር እንደሚታዘዙት ሁሉ ስለርሱ በመመስከርም ታዛዦች ለሚሆኑት መሆኑ እርግጥ ነው ። እውነተኛ እማኞች ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ቢኖራቸውም ይበልጥ የሚገለጠው ለሚ ታዘዙት ነው ። ከሁሉ ይልቅ የሚደሰቱትንና በመንፈስ የተሞላ ሕይወት እንዳላቸው ማስረጃ የሚሰጡትን ክርስ ቲያኖች ሳስብ ያላንዳች ቅሬታ ሁሉም ሌሎቹን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ይጥራሉ ።

## ሰዎችን ወደ ክርስቶስ በማምጣት የሚገኝ ደስታ ።

ለሁላችን ይህን ዓለም የደስታ ስፍራ ለማ ድረግ ከሚረዱት ነገሮች አንዱ ወንዶችና ሴቶች ደስ ባላቸው ጊዜ በፊታቸው ላይ የሚያበራ የደስታ ፈገ ግታ ነው ። በፊት ላይ የምትገለጥ ውስጣዊ ደስታን የሚሰጡ ብዙ ነገሮች አሉ ።

በሕይወቴ እንዳየሁት ከሌላ ምንጭ ከሚመጣ ደስታ ይልቅ እንዱን ኃጢአተኛ ወደ ክርስቶስ በመራ ሰው ፊት ላይ የሚታይ ደስታ ደማቅና እውነተኛ ነው እላለሁ ።

እስቲ መለስ ብለህ በእውነት ደስተኞች የሆኑትን ክርስቲያኖች እይ ። እነማን ናቸው ? ቀደም ብዬ እንደተናገርሁት እንዲሁ የሚሆኑት ፤ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የሚያመጡ ናቸው ።

## መጽሐፍ ቅዱስን መውደድ ።

ክርስቶስን በጣም የሚያውቁ መጽሐፍ ቅዱስን እጅግ በጣም ያፈቅራሉ ። አንድ ሰው « መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ፤ ጨለምለም ሲል ወደ ሰማይ አትኩሮ እንደመመልከት ነው » አለ ። ዓይኖቻችንን ስናነሣ ትኩር ብለን ስንመለከት ሰማይ እየተዘረጋ ፤ ከዋክብት እንድ ባንድ ቆየት ብለው ደግሞ እየበዙ እየበዙ ይታያሉ ።

እንደዚህም ሁሉ ቅዱስ ቃሉን እየተመለከትን እግዚአብሔርን ደጅ ስንጠና የእውነትንና የጸጋን ኮከብ እንደሚገልጽልን እውነት ነው ። ሲጽፉበት የማይታይ ቀለም አለ ፤ ነገር ግን በእሳት ፊት ሲያደርጉት ሙቀት ይሰማውና ጽሕፈቱ ወለል ብሎ ይታያል ። እንደዚህም ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ስናነብና ስንመለከት መንፈስ ገልጾ ያሳየናል ።



የማይጠራጠረው ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን ያፈቅራል ። መንፈሳዊ ምግቡና አጽናኙም ይሆናል ። አእምሮውን ለማነጽ ሌላ መጽሐፍ ቢያነብና ቢያጠናም ፤ ነፍሱን የሚያረካ አጥጋቢ ምንጩ ተንኰል የሌለበት የእግዚአብሔር የቃሉ ወተት ነው ። (ኢዮ. ፳፫ ፥ ፲፪ ።) በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል ። (መዝ. ፩ ፥ ፪ ።) ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት ላይ ሳለ ከሰማይ « ወደዚህ ውጣና ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚሆነውን ነገር አሳይሃለሁ » የሚል ድምጽ በሰማ ጊዜ « ወዲያው በመንፈስ እንደነበረ » ። እኛም መጽሐፍ ቅዱስን አፍቅረን ሲነበብ ፤ ሲተረጐም በሰማን ጊዜ ወይም ራሳችን ባነበብነው ጊዜ « ወዲያውኑ » ሁለንተናችን በመንፈሳዊ ነገር ይመሰጣል ።

## የጸሎት ሕይወት ።

ኢየሱስ ገና ወገግ ሳይል ተነሥቶ ወደ ጸሎት መሄዱን ባወቁ ጊዜ እነዚያ አራት ደቀ መዛሙርት እንዴት ተደንቀው ይሆን ? ( ማር. ፩ ፥ ፴፭—፴፯ ተመልከት ።)

ጸሎት ለነፍስ ትንፋሽ ነው ። መጽደቁንም ያወቀ ክርስቲያን ወዲያው የጸሎቱን ኃይል በራሱ ሕይወት ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ሕይወት ያያል ። እንደ ሰው ልጅ ( ክርስቶስ ) ለመማለድና ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ለማድረግ ወደ ተሠወረ ቦታ ይሄድና ሲመለስ እንደ ሙሴ ፊቱ እያበራ ይወጣል ። እንደማርታ

እህት እንደ ማርያም እሱን ለማገልገል ከሚያደርገው ጥረት ይልቅ አንድነት ከእርሱ ጋር ቢኖረው እግዚአብ ሔር እንደሚደሰት ያውቃል ።

## ክርስቲያን ጓደኞችን መውደድ ።

ከጥቂት ዓመታት በፊት ለክርስቲያኖች እንድ ናገር ተጠየቅሁና ንግግሬን እንደጨረስሁ እዚያ የተሰበ ሰቡ ሰዎች መዳናቸውን እንዴት እንዳወቁና እምነታቸው በምን እንደተመሠረተ የሚገልጽ አንድ ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስጡ ተባሉ ።

ከጥቂት ወራት በፊት አምኖ በጥርጥርና በፈ ተና ይቸገር የነበረ አንድ ነቃ ያለ ወጣት ፡ የመጽደቁን ማረጋገጫ መንፈስ ቅዱስ የሰጠው በ፩ ዮሐንስ ፫ ፡ ፲፬ የሚገኘው « እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለሆን ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሻገርን እናውቃለን » በሚለው እን ደሆነ ተናገረ ። ቀጥሎም የዚህን ጥቅስ እውነተኛነት እስ ኪያይ ድረስ ጥርጥር መከራውን ያሳየው እንደነበረ ነገ ረን ። ነገር ግን ይህን ጥቅስ ባስተዋለ ጊዜ ከሚሳደቡ ዓለማውያን ተለይቶ ከክርስቲያኖች ጋር ለመሆን እንደና ፈቀ ሲያስብ በእውነት ክርስቲያን መሆኑን ተረዳ ። ወን ድሞቹን ወደደ ።

እንዴት እውነት ነው ? የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ አንድነትን ይራባል ። ነገር ግን መንፈሳዊ አንድ ነት በዓለማውያን ዘንድ ስለማትገኝ ፈልጎ ፈልጎ ጌታን የሚወዱ ሰዎች ዘንድ ያገኛታል ።



እግዚአብሔር ለወገኖቹ ጽኑ ፍቅር ሰጥ ቷል ። « እርስ በእርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀ መዛ ሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ ። » ( ዮሐ ፲፫ ፡ ፴፭ ። )

## ኃጢአትን ማሸነፍ ።

ጸድቂያለሁ ብሎ ኃጢአትን አለማሸነፍ ሕማ መጥ መሆን ነው ። አንድ የማይቻለኝ ነገር አለ ኃጢ አትን ከመውደድ ካልዳንን በፍጹም አልዳንም ። በአፍ ብቻ ክርስቲያን ነኝ የሚልና በፍጹም ልቡ የሚያምን ክርስቲያን የሚታወቀው እዚህ ላይ ነው ።

ለመዳኑ እርግጠኛነት እየተሰማው ዓለምን በመ ውደድ በኃጢአት ላይ አሸናፊነትን የማያገኝ እንበ ቢኖር እንዲህ ልበለው ። አሸናፊው ክርስቶስ አዳኝህ ነው ። ውጊያውን ለእርሱ ብትለቅለት ፣ በመንፈስ ቅዱስ ይመላህና ድል አድራጊነትን ይሰጥሃል ። ሰይጣንን በመ ስቀሉ ድል አድርጎታል ። አንተም ብትፈቅድለት በሕይ ወትህ ድል ያደርግልሃል ። በዚያን ጊዜ ባንተ ውጊያ ሳይሆን ሰውነትህን ለክርስቶስ በማስገዛት ታሸንፋለህ ።

የክርስቲያን ኑሮ ከዓለማዊ ኑሮ እጅግ የተለየ ነው ። እንዲህ ካልሆነ አይሆንም ። የእግዚአብሔርን ልጅ ፊት ለፊት ተገናኝቶት አውቆታልና ማንም ሰው ቢሆን ኢየሱስን አይቶ ሳይለውጥ የሚቀር የለም ።

ትክክለኛን ነገር ለማድረግ ስለምንወድ በስሕተት እንደተጠመደ ልንቆጠር ነውን ? በጠላቶች ዘንድ የሚጠላውን መጽሐፍ ቅዱስን ስለምንወድ ተደርጐ የማይታወቅ ነገር አድራጊዎች የመባል ስም ሊሰጠን ነውን ? የሚደርስብንን መከራ ለምስጋና ቤታችን የሚሆን አዲስ ሰው የምንሠራበት ነገር አድርገን ብንመለከተው ፣ ይፈረድብናልን ? ሌሎቹ እንዲድኑ ጸንተን ብንመስክር መቀለጃ ልንሆን ነውን ? ሰዎች የእግዚአብሔርን መኖር ሲጠራጠሩ ፣ « እንዴት ከእግዚአብሔር ጋር ሊነጋገሩ ይችላሉ » ብለው ይገረሙብን ይሆን ?

ለዓለም አንቆቅልሽ ሆነን ። ነገር ግን አንድ ነገር ሆነናል ። እግዚአብሔርን አናውቀዋለን ፣ አውቀንውም አናፍርበትም ።

## መደምደሚያ ።

## በጸጋ እድገት አስፈላጊ ምሥጢራት ።

በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ እንድትሆን አሳስብሃለሁ ። መጽሐፍ ቅዱስን ከዚህ በታች እንደተገለጸው አድርገህ አንብብ ።

፩. መንፈስ ቅዱስ እንዲመራህ ፈቅደህ መጽሐፍ ቅዱስን አንብብ በሌሎች አርዳታ ብዙ አትታመን ።

፪. በጸሎት መንፈስ አንብብ ።



፫. በመታዘዝ መንፈስ አንብብ ። (ብዙ ብርሃን ለመቀበል ብትፈልግ ለተገለጸልህ ብርሃን አስቀድመህ መታዘዝ ይገባሃል ። )

፬. በትዕግሥት አንብብ በምታነብበት ሥፍራ አስቸጋሪ ጥያቄ ቢመጣብህ ብዙ አትጨነቅ ምክንያቱም አንድ ቀን በሌላ ክፍል ስታነብ መልሱን ታገኘዋለህ ።

አንድ ሊቅ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ « ዋናው ጥያቄ ስንት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ዘልቀኸዋል ? አይደለም ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስንት ጊዜ ዘልቆሃል ነው ። »

ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ብቻ ሳትሆን የክርስቲያን መጽሐፎችንም በትጋት የምታነብ ሁን ። በክርስቲያኖች ቤት ከሚገኙት አሳዛኝ ነገሮች አንዱ የሚነበቡ የክርስቲያን መጽሐፎች እጦት ይመስለኛል ። እምን መጽሐፍ ቅዱስ አዘያው አለ ፣ ግን ከውስጠኛው ይልቅ የውጭው አርጅቷል ። የጋዜጣ ማስቀመጫውን የዓለም ጋዜጦች ሲሞሉት ፤ በብዙ ሺ በሚቆጠሩ ክርስቲያኖች ቤት ፤ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚረዳ መጽሐፍ ወይም የክርስቲያን ጋዜጣ ፤ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ እንኳን የለም ፤ ልጆችም በለመንፈሳዊ ነገር ሳያውቁ ያድጋሉ ። አበክህ ያንተም ቤት እንደዚህ እንዳይሆን አስብበት ።

ጳውሎስ ጢሞቴዎስን «ማንበብን አዘውትር» አለው ። ( ፩ጢሞ. ፬ ፡ ፲፫ ። ) በሮም ታሥሮ ሳለ « መጻሕፍቱን ይዘህ ና » ብሎ ጻፈለት ። ( ፪ጢሞ.፬ ፡ ፲፫ ። )

ምንም ድህነት ቢዘዛ ራዲዮ መግዛት ያቅተው እንጂ ጥሩ ጥሩ መጻሕፍትና ጋዜጦች ለመግዛት የሚጭ ገር የለም ። መግዛት የሚያስፈልጉህን የክርስቲያን መጻ ሕፍት ጥቂቶቹን ከዚህ ቀጥሎ እጽፍልሃለሁ ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማውጫ ።
የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ሮሜ ።
መሪ ብርሃን ለመንገደኛ ።
የመንፈስ ሰይፍ ።
መጽሐፍ ቅዱስን እናጥና ።
መንፈሳዊ ምሥጢራት ።
ደማቂቱ ከተማና መንገዱዋ ።
፳፬ መንፈሳዊ ታሪኮች ።
ወዳጄ ልቤ ።
የመጽሐፍ ቅዱስ ትንሽ መክፈቻ ።

የሚነበቡ ብዙ የክርስቲያን መጻሕፍት በእን ግሊዘኛም በአማርኛም እንዳሉ ታውቃለህን ። አንድ ሰው እንዲህ ሲል ተናገረ « አንድ ሰው የሚያነበውን አሳየኝና ምን ዓይነት ሰው እንደሆን አሳይሃለሁ ። »



የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማውጫና የመጽ ሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚሰጥህ ጥሩ መጽሐፍ እንዲኖርህ ያስፈልጋል ። ዋጋቸው በጣም ቀላል ከመሆኑ በላይ ለመንፈሳዊ ዕድገት በጣም የሚጠቅሙ ናቸው ።

ወደየትኛው ቤተ ክርስቲያን ትኼዳለህ ? አዘ ውትረህ ትሄዳለህ ? ለክርስቶስ እንድትቆም አዘውትረህ መሄድ ይገባሃል ። በውነትም የማይጠራጠር ክርስቲያን ከሆንህ እዚያ ማገልገል ይገባሃል ።

የምጽሐፍ ቅዱስን መሠረታዊ እውነት የሚ ክዱ ጓደኞችህ ወይም ቤተ ሰዎችህ ዘመን አመጣሽ የሆነ ነገር ቢነግሩህ ፈጽሞ አትስማ ስመቃወምም አትፍራ ። ትሁት በመሆን የክርስቶስን እውነተኛ መንፈስ ትገልጥ ዘንድ አሳተኛ ትምህርትን በግልጽ ተቃወም ። አእምሮ ህን ለእውነት የተከፈተ ለሐሰት የተዘጋ አድርግ ። የጌታ ደስታ ብርታትህ ይሁን ። ራስህን ዝቅ ዝቅ ክርስቶስን ከፍ ከፍ አድርግ ። « እኔ አምናለሁና የዚህ ዘመን መከራ የሚመጣውን ክብር እንዳይተካከለው ። በኛ ይገ ለጥ ዘንድ ያለውን ። » ( ሮሜ ፩ ፡ ፲፮ ። )

<u>የመጨረሻ ቃል ።</u>

ዛሬ የማይጠራጠር ክርስቲያን ልትሆን ትችላ ለህ ። አሁን በዚህች ደቂቃ በእውነተኛ ልብ ወደ እግ

ዚአብሔር ለመመለስ ፈልገህ እንደሆን ፤ በትህትና እን
ዲህ ብለህ ጸልይ ።

የተወደድህ ሰማያዊ አባት ሆይ ፤
እንዱ ልጅህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያስ
ፈልገኝ መድህን መሆኑን አምኜ በልቤ አሁን እቀበለዋ
ለሁ ። እንደቃልህ የዘላለምን ሕይወት አሁን ይሰጠኛል
ብዬ አምናለሁ ። እውነተኛ ክርስቲያናዊ ሕይወት እን
ድኖር ጸጋና ብርታትን ስጠኝ ። በኢየሱስ ስም አሜን ።